
# የ፫ኛው ፓትርያርክ በዓለ ሢመት

# THE ENTHRONMENT OF THE THIRD PATRIARCH



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

**HIS HOLINESS ABUNE TEKLE HAIMANOT**
**Patriarch Of The Ethiopian Orthodox Church**

www.ethiopianorthodox.org

# የ፫ኛው ፓትርያርክ በዓለ ሢመት

**አዘጋጅ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

የስብከተ ወንጌልና ማስታወቂያ መምሪያ ።

**አዲስ አበባ**

ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም.

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org

| አርእስት | ማ ው ጫ | ገጽ |
|---|---|---|


| | | |
|---|---|---|
| ፩ኛ | (ርእሰ አን ቀጽ) ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ፭ |
| ፪ኛ | የብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሕይወት ታሪክ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ከ፱—፲፭ |
| ፫ኛ | ስለ ምርጫው ይዘት ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ከ፲፯—፲፱ |
| ፬ኛ | የብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኤጲስ ቆጶስነት ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ከ፳—፳፫ |
| ፭ኛ | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ከ፳፬—፳፯ |
| ፮ኛ | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምግባረ ሠናይ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ከ፳፰—፳፱ |
| ፯ኛ | የውጭ ግንኙነት ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ከ፴—፴፭ |
| ፰ኛ | የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ተሐድሶ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ከ፴፯—፵፩ |
| ፱ኛ | ወጣቶች በተሐድሶ ያላቸው ድርሻ ምንድርነው? ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ . . | ከ፵፩—፵፪ |
| ፲ኛ | ከክርስቲያናዊ ተራድኦ ጽ/ቤት የተገኘ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ከ፵፫—፵፰ |
| ፲፩ኛ | ስለ ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የፓትርያርክነት ታሪካዊ ምርጫ የተደረሱ ቅኔዎችና ግጥሞች ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ከ፵፰—፵፱ |


www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ፫ኛው ሢመተ ፓትርያርክ

እስከ ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትመራ የነበረው ከግብጽ ይላኩላት በነበሩት ጳጳሳት ነው ። በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ምዕመናን ትግል ምክንያት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ይሾሙላት ጀመር ።


በመጨረሻም ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ በግብጽ ቤተ ክርስቲያን ተሾሞ ፓትርያርኩ ጳጳሳትን በሀገር ውስጥ እንዲሾም ተደረገ ። ከዚያም በኋላ በኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ሿሚነት የኢትዮጵያ ጳጳስ ለመጀመሪያ ጊዜ ፓትሪያርክ ሆኖ ተሾሟል ።

ዛሬም ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሦስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ተሾመዋል ። የዛሬው የፓትሪያርክ የሹመት በዓል ከዚህ ቀደም ከነበሩት የሹመት በዓሎች ሁሉ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ይለያል ።

፩ኛ/ ዛሬ ለሦስተኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው የተሾሙት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከዚህ ቀደም ይደረግ እንደ ነበረው በመሳፍንት ፣ በመኳንንትና በመንግሥት ባለሥልጣኖች ትእዛዝና ተጽእኖ የተመረጡ ሳይሆን ከ፳፱፻፷፮ ወረዳዎች በተውጣጡ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ምእመናን በሕዝቡና በቤተ ክርስቲያንየተወከሉ መራጮች ቅዱስነታቸው በሐዋርያነት በሚያገለግሉበት ጊዜ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለሕዝብ የሠሩትን መልካም ሥራ አይተው ለመሪነት ብቁ መሆናቸውን አምነው በዲሞክራሲያዊ መንገድ ስለመረጧቸው ።

፪ኛ/ የዛሬውም ሹመት እንዳለፈው ጊዜ ለዝናና ለመታወቂያ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያናችን በአመራር ተሐድሶ ላይ ስለሆነች የተጀመረውን የተሐድሶ ዕቅድ ከግቡ ለማድረስ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ቃል ኪዳን የሚገቡበትና ቤተ ክርስቲያንንም አሁን ካለችበት የተመሰቃቀለ የአስተዳደር ሁኔታ ለማውጣት በሚያደርጉት ትግል እንዲረዳቸው ሕዝበ ክርስቲያኑን የሚጠይቁበት ዕለት ነው ።

ስለዚህ የዛሬው በዓለ ሢመት የቃል ኪዳን በዓልና ቤተ ክርስቲያናችን ወደ ተሐድሶ ግቧ ለመድረስ ከምዕመናን ጋር ጉዞዋን የምትጀምርበት ዕለት ነው ።



አባ መልአኩ ወልደ ሚካኤል ።

www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሕይወት ታሪክ ባጭሩ

ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በ፲፱፻፲ ዓ/ም ከአባታቸው ወ/ር ወልደሚካኤልና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዘውዲቱ ካሣ ተወለዱ ፤ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በመካነ ልደታቸው ጥንታውያን የኢትዮጵያን መጀመሪያ ደረጃ ትምህርተ ንባብ ፤ ቁም ጽሕፈትና ዜማ ተማሩ፤ከዚያም ለከፍተኛው ጥንታዊ ትምህርት በዘር ዘር ቅ/ሚካኤል ብቸና ጎጃም ሄደው ከመምህር ጥዑመ ልሳን ቅኔ ተማሩ ።

በ፲፱፻፳፮ ዓ/ም ከጠላት ወረራ በፊት ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ወደሲዳሞ ክፍለ ሀገር ወደ ወላይታ አውራጃ በደብረ መንክራት ተክለ ሃይማኖት ገዳም ማርይስሐቅንና መጽሐፈ መነኮሳትን ፤ ሌሎችንም የመጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ የብሉይና የሐዲስ መምህር ከነበሩት ከደብረ መንክራት ገዳም አበምኔት ከመምህር ወልደ ኢየሱስ ተምረዋል ። በዚህም ጊዜ የገዳሙ ንብረት ጠባቂ በመሆን ለብዙ ዓመታት አገልግለዋል ።

ብፁዕነታቸው በሚማሩበትም ሆነ በሚያስተምሩበት ጊዜ ከምእመናን እርዳታ በመጠየቅ ወገን የሌላቸውን ተማሪዎች ይረዱ ነበር ፤ ከዚህም በስተቀር ለሚያስተምሩአቸው ዕጓለ ማውታዎች ነጻ የመጻሕፍት ስጦታና ለገዳሙም የንዋየ ቅድሳትና የአልባሳት ልግስና ያደርጉ ነበር ። ራሳቸው የሚተዳደሩበት ግን ተክል በመትከል በወዛቸው ነበር ።

ብፁዕነታቸው ያለምንም ደመወዝ በወላይታ በሚገኙት በሰባቱ ወረዳዎች እየተዘዋወሩ በሚሰጡት የወንጌል ትምህርት ሕዝበ ክርስቲያኑ ስለረካና ስለ ወደዳቸው አባትነታቸውንም ስለተቀበለው በምክራቸው ከምዕመናን በተሰበሰበ ያስተዋጽኦ ገንዘብ ፷፰ አብያተ ክርስቲያናት ፷፱ ት/ቤቶች አሠርተዋል ። ለአብያተ ክርስቲያናቱም ሆነ ለት/ቤቶች ማሠሪያ ወጭ የሆነው ገንዘብ የምእመናኑ



አባታችን ከአሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት አንዷ የቦዲቲ ምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ጉልበት ሳይታሰብ ከ፫፻ሺ ብር በላይ እንደሆነ ተገምቷል ። በ፷፱ቱም ት/ቤቶች ውስጥ የሚኖሩት ተማሪዎች ሥጋውዊውንና መንፈሳዊውን ትምህርት አጣምረው ይከታተሉ እንደነበር ታውቋል ። የብፁዕነታቸው ተግባር በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም ፤ በሶዶ ከተማ በደብረ መንክራት ተክለ ሃይማኖት ገዳም አካባቢ ፲፩ ክፍል የድኩማን ቤት በማሠራት ራሳቸውን ለመርዳት የማይችሉ ዱኩማንን ምግብና መጠለያ እንዲያገኙ አድርገዋል ። እንዲሁም በዚህ ከተማ ውስጥ ከ፬፻ ያላነሰ ሕዝብ በአንድ ጊዜ መያዝ የሚችል የወጣቶች የመጽሐፍ ቅዱስ አዳራሽ አሠርተው በአገልግሎት ላይ ይገኛል ። እንዲሁም አንድ ክሊኒክ



www.ethiopianorthodox.org



የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ።

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕነታቸው የገዳማት  አበ ምኔቶችን ሲቀበሉ ።

## የብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሕይወት ታሪክ ባጭሩ

ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም/ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በተከናወነው የምርጫ ሥነ ሥርዐት ተጠባባቂው ፓትርያርክ የሲኖዶስ አባሎችና ከየወረዳዎች የመጡት ፰፻፱ መራጮች ተሳትፈዋል ።

የድምፅ አሰጣጡ ሥነ ሥርዓት ከላይ በተጠቀሰው ቀን ከጧቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ቆይቷል ። በመጨረሻም ተጠባባቂው ፓትርያርክ፣የአስመራጭኮሚቴ አባሎች፣የመንግሥት ተጠሪዎች፣የሕግ ታዛቢዎች በተገኙበት የምርጫው ካርድ ተቆጥሮ ብፁዕ አቡነ ተክለሃይማኖት ፫፻፲፯ «ሦስት መቶ አሥራ ሰባት ድምፅ» በማግኘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነዋል ።

ይኸው ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን ዜና ማሠራጫዎች በከፍተኛ ደረጃ ተገልጧል ።

ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት ያላቸው ፤ ትኅትናን ወይም ግብረ ገብነትን ከትጋት ጋር አስተባብረው የያዙ ፤ ለጾምና ለጸሎት እንጂ ለመብልና ለመጠጥ የማይገዙ፤ለመንፈሳዊ ሥራ መትጋት ወይም ቤተ ክርስቲያንንና ት/ቤትን መኅብኘትን የሚወዱ ከመሆናቸውም ጋር በመልካም ምሳሌነታቸውና በጣዕመ ስብከታቸው ምእመናንን በመንፈሳዊ ሕይወት የሚገነቡ ፤ ስለሰላም የሚጥሩ ፤ ስለጽድቅ የሚራቡ ስለሆኑ ሐዋርያ ሆነው ይሠሩበት በነበረው አውራጃ ምእመናኑ ትምህርታቸውን በፍጹም ልብ ተቀብለው ገንዘብ በማዋጣት አብያተ ክርስቲያናትንና ት/ ቤቶችን ሌሎችንም የምግባረ ሠናይ ድርጅቶችን በብዛት ለመሥራት የቻሉመሆናቸውን በወላይታ አውራጃ ምእመናን እንዲሁም የብፁዕነታቸውን ሥራ በጎበኙ ሰዎች ዘንድ ይነገራል ።

የብፁዕ አቡነ ተክለሃይማኖት መንፈሳዊነት ተጨባጭ በሆነ ተግባር እንጂ የብሕትውና ልብስ በመልበስ አይደለም ፤

ሐዋርያነትን በሥራ የተረጎሙ እንደ መሆናቸው መጠን ለሕይወታቸው ዕረፍትን ሳይሹ በአንድ ቀን በእግራቸው በሦስትና በአራት ወረዳዎች እየተዘዋወሩ የቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን ችግር በመመልከት ለአውራጃና ለወረዳ አስተዳዳሪዎች አቤቱታ እያቀረቡ ራሳቸውም በሚሰጡት ስብከት ሕዝበ ክርስቲያኑን በጉልበትና በአስተዋጽኦ እያስተባበሩ የቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን ችግር ማቃለል የዘወትር ተግባራቸው ነው ። አስተዋይና ፈሊጠኛ ከመሆናቸውም በላይ በአካሄዳቸውም ሁሉ ፋናቲክነት ስለሌላባቸው ራሳቸው በትንሽ ጣታቸው መንካት የማይችሉትን ለምእመናን ማሸከም የማይወዱ በአስተሳሰባቸው ከዘመናዊው አስተሳሰብ ጋር አብረው የሚራመዱ መሆናቸውን የሚያምንበት ተግባራዊ ሐቅ ነው ።

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ሁሉ አብያተ ክርስቲያናትንና ት/ ቤቶችን በማሠራትና በማስተዳደር እንዲሁም መምህራኑንና ተማሪዎችን በመቈጣጠር«የምግባረ ሠናይ ድርጅቶችን በማቋቋምና የመገበሪያ ቦርድ» ተብሎ ይጠራ እንደነበረው ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮችን በመፍጠር በጠቅላላው «እነ ብርሃን ሕይወትን»የመሳሰሉ የመንፈሳዊ ማኅበራትን በማቋቋምና ሌሎችንም መንፈሳዊ ግዳጆችን በመፈጸም ረገድ እውነተኛ ሐዋርያ ስለሆኑ ለቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደምብ ሆኖ የወጣው ቃለ ዐዋዲ ትርጒም ሊኖረው የሚችለው በእሳቸው ዘንድ መሆኑን ለአያሌ ዓመታት አብረዋቸው የሠሩ አያሌ ሰዎች ይመሰክራሉ ።

የ፲ኛው ፓትርያርክ በዓለ ሢመት

# ስለምርጫው ይዘት በሀገር ውስጥና በውጭ አገር የተላኩ አስተያየቶች ፥ ቴሌግራሞችና ፤ የደስታ መግለጫዎች

ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክነት መመረጣቸውን ምክንያት በማድረግ አራት የአብያተ ክርስቲያን መሪዎች የደስታ መግለጫ ቴሌግራም ያስተላለፉ ሲሆን እነሱም በኢንግላንድ የካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ የእስታንቡል ፓትሪያርክ በሮና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና የቡካሬስት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው ። የየአብያተ ክርስቲያናቱ መሪዎች ስለ አዲሱ ፓትርያርክ መመረጥ የተሰማቸውን ደስታ ከመግለጻቸውም በላይ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የወደፊት እድገትና መሻሻል ያላቸውን መልካም ምኞት በየበኩላቸው ገልጸዋል ።

** ** **

ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለሦስተኛ ጊዜ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ስለተመረጡ ከልዩ ልዩ ድርጅትና ግለሰቦች አያሌ የደስታ መግለጫ መልእክቶች በደብዳቤና በቴሌግራም ተላልፈዋል ፤ ለተላለፉትም የደስታ መግለጫ መልእክቶች ብፁዕነታቸው ተመሳሳይ መልስ ሰጥተዋል የተላለፉትም የደስታ መግለጫ መልእክቶች ከዚህ ቀጥሎ ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹ ቀርበዋል ።

** ** **

ሐምሌ ፪ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም/ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክነት ለተመረጡት ለብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፤

<u>አዲስ አበባ</u>

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክነት በመመረጥዎ እንኳን ደስ አለዎ እያልኩ የተሰማኝን ታላቅ ደስታ ልገልጽ እወዳለሁ ። ለተመረጡበት ታላቅ የኃላፊነት ቦታ ሥራዎን በሚገባ ለማከናወን ይችሉ ዘንድ ሙሉ ጤንነት አግኝተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያሰበልዎትን ሁሉ ከፍጻሜ እንዲያደርሱ እመኝልዎታለሁ ።

በቅርቡ ተገናኝተን አሳብ ለአሳብ እስክንለዋወጥ ድረስ በጸሎቴ አስብዎታለሁ ።

በክርስቶስ ወንድምዎ አቡነ ራይመንድ

ዴቴል ዶርፍ

የባቲካን አምባሳደር

* * *

ሐምሌ ፪ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ለታላቁ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ለተጠሩ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት የሰሎሞን ጥበብና የሐዋርያት ፍጹምነት መመሪያዎ እንዲሆን እንመኛለን ።

ልጆችዎ መ/ጳውሎስ ቀጸላ

ዲ/አስተርአየ ጽጌ

አዋሳ

* * *

ሐምሌ ፪ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለፓትሪያርክነት በመመረጥዎ እንኳን ደስ ያለዎት ። እኔጥንት በርስዎ የበላይ ጠባቂነት የቤተ ክህነትን ትምህርት በመከታተል ላይ የነበርኩና አሁንም በአንዳንድ የሥራ መደብ ላይ



www.ethiopianorthodox.org

የምገኝ የጥንት ተማሪዎ ለፓትሪያርክነት በመመ ረጥዎ ለደስታዬ ወሰን የለኝም ፈጣሪያችን አዲሱን ሥራዎን እንዲያቃናልዎት እለምናለሁ ።

የማነ ብርሃን ቸርነት

* * *

ሐምሌ ፬ ቀን ፲፱፻፰፰ ዓ/ም ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ትክክለኛ እውነተኛ አባት በመሆንዎ ሕዝቡ ይህንኑ ተገንዝቦ ለፓትሪያርክነት ስለ መረ ጠዎ የተሰማኝ ደስታ ከፍ ያለ ነው ።

ሲሳይ አየለ

ነገሌ ቦረና

ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፰፰ ዓ/ም ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ለተደረገው የ፫ኛው ጊዜ የፓትርያርክነት ምርጫ የመመረጥ ዕድል በመ ጎናጸፍዎ የደስታው ተካፋይ በመሆን የተሰማኝን ከፍ ያለ የደስታ መግለጫየን በልዑል እግዚአብሔር ስም እያቀረብኩልዎ ወደ ፊት የሚጠብቅዎ ታላቅ የሥራ ኃላፊነት የተቃና እንዲሆንልዎ እመኛለሁ ።

ላቀች ፋንታው

ወላሞ ሶዶ

** ** **

ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፰፰ ዓ/ም ለብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን አባት ፤

አዲስ አበባ ፤

ብፁዕ አባታችን ፤

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓት ርያርክ ሆነው በመመረጥዎ እንኳን ደስ አለዎ እያልኩ የተሰማኝን ታላቅ ደስታ ልገልጽ እወዳ ለሁ ። ተስማሚ በሚሆን ጊዜም መጥቼ ለማነጋገር እንደምችል ተስፋ አደርጋለሁ ። ሰላም ለአባት ነትዎ ይሆን ዘንድ እመኛለሁ ።

ዲ - ኤም - ዴይ

የእንግሊዝ አምባሳደር

# ብፁዕ አቡነ ተክለሃይማኖት

## ለደስታ መ/የሰጡት መልስ

ከልዩ ልዩ ድርጅቶችና ግለ ሰቦች በቴሌግራምና በደብዳቤ ለተላለፉት የደስታ መግለጫ መልእክ ቶች ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መልስ ሰጥተዋል ።

በቸሩ ፈጣሪያችን ቅዱስ ፈቃድ በመላው ካህ ናትና ምእመናን ፍላጎት መሠረት ለዚህ ታላቅ ቦታ በመመረጤ የላካችሁልኝ የደስታ መግለጫ መልእክት ደርሶኛል ።

የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በሁላችንም ላይ አድሮ ለቤተ ክርስቲያናችን ዕድገትና መሻሻል በኅብረት ለመሥራት ያበቃን ዘንድ የዘወትር ጸሎቴ ነው ።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ ።

ብፁዕ አቡነ ተክለሃይማኖት

## የጋዜጦች አስተያየት

አዲስ ዘመን ፴፯ ዓመት ፣ ቍጥር ሺ ፶፯
ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፰፰ ዓ/ም

| ር እ ሰ አ ን ቀ ጽ ። |
|---|

## ዲሞክራሲ በሥራ ላይ

የሰሞኑ አንድ አስደናቂ ዜና የኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ፓትሪያርክ ምርጫ ነው ሊባል ይቻላል ። ስለምርጫው አፈጻጸም የተሰ ጠው መግለጫ በመላ ኢትዮጵያ በሚገኙት አም ስት መቶ ስድሳአምስት ወረዳዎች የሚኖሩ ምዕ መናንና አሥራ ዘጠኝ ጥንታዊ ገዳማትን የሚወ ክሉና እንዲሁም የሲኖዶስ አባሎች ተካፋይ የሆ ኑበት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓት ሪያርክ አመራረጥ ታሪክ የመጀመሪያው ዲሞክራ ሲያዊ ምርጫ ነው የሚል ነበር ። መሆንም አለበት ። በእርግጥም ውጤቱ ታየ ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶ ክስ ቤተ ክርስቲያን ሦስተኛው ፓትሪያርክ ሆነው የተመረጡት ካሁን ቀደም በቤተ ክህነት የገዥ መደብ አካባቢ ስማቸው ያልታወቀ ደበሎ የሚለብሱ



www.ethiopianorthodox.org

ጫማ የማያደርጉ አንድ ተራ ሐዋርያ የነበሩ ናቸው ። ፎቶግራፉን የተመለከቱ ብዙ ሰዎችም ተደንቀዋል ። የደነገጡም የበረገጉም አይታጡም ሌላ ምልክት ያሳያቹዋልና ።

ያለፉት የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ፤ ምርጫ የፊውዳሉ መደብ የጥቅም ተባባሪዎቹን የሚጠቃቅስበትና የሚመለምልበት ኢምፔሪያሊዝምም «በአሰልጣኝነት» ስም አብሮ የሚሰለፍበት የጭቆና ሰይፍ በመስቀል የሚባርክበት መስቀል የጭቆና ሰይፍ የሚያነግትበት ባጭሩ ገገር መደቦች ሰፊውን ሕዝብ ሰማይ ሰማይ እያሳዩ በገዛ ሃይማኖቱ መልሰው የሚጨቁኑበትን መሣሪያ የሚያዘጋጁበት ሥርዓት ነበር ። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች አካባቢ የወጣው የሚዘገንን ጉድ ማስረጃ ነው ።

ከዚህ ላይ ቁም ነገሩ የአዲሱ ፓትርያርክ ጫማ ማድረግና አለማድረግ አይደለም ። ቁም ነገሩ ፤ « ስለሃያኛው ክፍለ ዘመን ሰፊ አስተያየት ያለው ፤ በዓለም አቀፍ ጉባኤ ቢያቀርቡት በአለባበሱ የሚያኮራ በአነጋገሩ የሚረታ በዘመኑ ትምህርት» የበቃ እየተባለ ከፊውዳሉ ሥርዓት ጋር እንደባልና ሚስት ተቃቅፈው በልክ እንደተሠራ ጫማ ተስማምተው እንደብቅልና ጌሾ ተዋሕደው የነበሩትን መልሶ ለመተካት የተደረገውን ሙከራ በማክሸፍ የምዕመናኑ ተወካዮች ሥራቸውንና ብቃታቸውን ብቻ በመለካት የመሰላቸውን መሪ መምረጣቸው ነው ። ይህም የሰፊው ሕዝብ ንቃተ ሕሊና ከፍ እያለ መሔዱን ያሳያል ።

በየካቲት የፈነዳው አብዮታዊ ማዕበል ወደፊት እያጥለቀለቀ ሲሔድ የማይነካው ድርጅትና ተቋም የለም ። የማይዳስሰው የማይለውጠው ያረጀና ያፈጀ አስተሳሰብ የለም ። የማያንኳኳው በር የለም ። ከአብዮቱ ሂደት አንዱ ዋና ምዕራፍም የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት አቋም በጥንቃቄ መለየት በሃይማኖቶች ላይ ልዩነትና አድልዎ አለማድረግ ነው ። በዚህም የአብዮት ድል ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ምዕመናን ለመጀመሪያ ጊዜ ያለተጽዕኖ ፓትርያርካቸውን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ሊመርጡ ችለዋል ። ምርጫቸው ከእነርሱ «የገዥ መደብ» ውጪ የሆነውን ሁሉ» ምናምንቴና ጥርቃሞሽ » እያሉ ይመጻደቁ የነበሩ ትን ፊውዳሎች ቅስም የሚሰብር ነው ። እንግዲህ ሰው የሚለካውና የሚመረጠው በሌላ መሆኑን አረጋግጠላቸዋል ። እንደ ዘውዱ መገርሰስ ፤ እንደገጠሩ መሬት የሕዝብ መሆን ይህም ምርጫ ሌላው ተጨማሪ መርዶዋቸው ነው ።

ይህ የሰሞኑ ምርጫ ወደፊት ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚካፈልበትን ዋና ምርጫ ያስታውሰናል ። ይኸውም በፊውዳሊዝም በኢምፔሪያሊዝምና በቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም መቃብር ላይ የሚቋቋመው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፣ ነው ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጽ «የሰፊው ሕዝብ ትግል ተደራጅቶና ገፍቶ ሕዝባዊ ግንባር እንደተቋቋመ በትግሉ ውስጥ የተሳተፉት የግንባሩ አባል ፓርቲዎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ከሚያቀርቧቸው ምልምሎች መካከል ሕዝቡ በሙሉ ነጻና ምሥጢራዊ በሆነ ምርጫ እንደራሴዎቹን መርጦ የመንግሥቱን ከፍተኛ ሥልጣን ወደሚይዘው አብዮታዊ ሸንጎ ይልካል . . . . ይላል ። »

ግልጽ ነው ። ትግሉ መቀጠል አለበት ። መደራጀቱ መፋጠን አለበት ። ሰፊው ሕዝብ እየተደራጀም ፤ ወዳጅና ጠላቱን ከአሁኑ እየበጠረ መሔድ አለበት ። በተለይ ግንባር ቀደምትነቱን የሚይዘው የወዝ አደሩ ክፍል ከአሁኑ በድርጅት አመሠራረቱ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አብዮታዊና ብሔራዊ ግዴታው ነው ። መሠረቱ ከተበላሸ ግድግዳና ጣራው ዋጋ አይኖረውም ።

## ዜና ቤተ ክርስቲያን

ሦሳሳኛ ዓመት ቍ/ ፵፰ ሐምሌ ፬ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም

## በሥራ መመረጥ

በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊው ዓለም የሰው ልጆች ከራሳቸው መካከል የተሻለውን ሰው ለተሻለ ሥራ ለመምረጥ የሚሞክሩት በብዙ አቅጣጫዎች ነው ። እነዚህም የተለያዩ አቅጣጫዎች እውቀት፣ ሥራ ፣ ብልጽግና ፣ ተዘምዶና ግርማ ርእየት ሲሆኑ በእነዚህ ሁሉ የምርጫ መስኮች እየተመረጡ አያሌ ሥጋውያንና መንፈሳውያን መሪዎች በሥልጣን ላይ ሲቀመጡ ይኖራሉ ። ከተዘረዘሩት የምርጫ መለኪያዎች ሦስቱ ማለት ብልጽግና ተዘምዶና ግርማ ርእየት መራጮችን ወገን በራሱ ላይ እባብ ሲያስጠመጥሙትና የኑሮ ህልውናውን ሲያቃውሱበት የኖረ ሰብአዊ ድርጊቶችና መቅሠፍት ሕዝብ ናቸው ። እነዚህን ተመርኩዘው የተመረጡና የመረጡ ሁሉ ዝክረ ስማቸው በታሪክ ፊት የተደመሰሰ ከመሆኑም በላይ በመጭው ትውልድ ዘንድ የዘለዓለም ተወቃሾች ስለሆኑ አጽማቸው እንኳ በመቃብር ዕረፍት ሊያገኝ አይችልም ።



www.ethiopianorthodox.org

በሀገራችን በኢትዮጵያ ባለፈው መንግሥት ባላባታዊ ሥርዓት በእውቀታቸውና በሥራቸው ከሚመረጡት ሰዎች ቁጥር ይልቅ በመልከ ቀናነት ፣ በሀብት ፣ በዘርና፣ በጎሣ የሚመረጡት ሰዎች ቁጥር እጅግ የበረከተና የበዛ እንደ ነበር ከማንም የተሰወረ ምሥጢር አይደለም ። ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በመላ ኢትዮጵያ ከሚገኙት ልዩ ልዩ የሥራ ድርጅቶች አንዷ በመሆኗ አድኃሪው ሥርዓት ስለሚነካት በመንፈሳዊ ኃላፊነት የሚሾሙላት አበው ሥርዓተ ሢመት ሁሉ የሚፈጸመው በዚህ ዓይነት ዘዴ ስለ ነበር ዝቅተኛውና ጭቁኑ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንደ ወትት ሲናጥና ሲገፋ ላቡንም ያለ አግባብ ሲበዘበዝ ያሳለፈው የሚያንገፈግፍ የመከራ ጊዜና የደረሰበት ስቃይ በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ሆነ በትውልድ ሕሊና ለዘለዓለም ተቀርጾ የሚኖር የማይረሳ የዓመጽ ትዝታ ነው ።

በእውቀትና በሥራ መመረጥ የተሻሉ ምርጫዎች ቢሆኑ ቅሉም ከሥራ የሚበልጥ እውቀት ስለሌለ ማወቅም ለመሥራት በመሆኑ እውቀት አላቸው ተብለው ከተመረጡ በኋላ እውቀታቸውን በተግባር ገልጠው ከማያሳዩ ዝንጉዓን ይልቅ እውቀታቸውን በሥራቸው የሚያስመሰክሩ ትጉሆችን ለተመረጠ ሥራ መምረጥ ተመራጮችን መጥቀምና መርዳት ሳይሆን የሚመረጡበትን ከፍተኛ ዓላማ መምረጥና ማክበር እንደሆነ መገንዘብ የመራጩ ወገን ዓይነተኛ ተግባር ነው ። ይህም በመሆኑ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓ/ም በተፈጸመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ምርጫ«ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ»በተባለው መሠረት ሥራቸው በሰው ፊት ያበራው የአባ መልአኩ ወልደ ሚካኤል ለፓትርያርክነት መመረጥ የመራጩን ወገን የመንፈስ ንቃትና የሞራል ዕድገት የሚያሳይ ጉልህ መነጽር ነው ።

ደጋግመን እንደገለጥነው ሁሉ ሊቃውንትና ምእመናን በነጻ አሳብና በዲሞክራሲ መንፈስ እየተመሩ ያለምንም አድልዎና ተጽእኖ መንፈሳዊ አባታቸውን ለመምረጥ ባደረጉት ትብብርና ባሳዩት በጎ ፈቃድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዓምድ የመጀመሪያ የሆነው የአባ መልአኩ ወልደ ሚካኤል ለሦስተኛ ጊዜ ፓትርያርክነት መመረጥ በዘመናት መካከል ከተፈጸሙት ታላላቅ ተአምራት እንደ አንዱ የሚቆጠር ታላቅ ተአምር ነው ። እኒህ ትጉሕና ሐዋርያነታቸውን በገሃድ ያሳዩ ትሩፈ ምግባር አባት የተገኙት ከጭቁኑ ካህን መካከል ስለሆነ የእሳቸው መመረጥ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በወዝ አደሩ ድል አድራጊነት በመካሄድ ላይ ላለው የሀገራችን አብዮት የመጀመሪያ መተርጉምና ተቀዳሚ ምሳሌ እንድትሆን አድርጓታል ።

የትሑትና የትጉሑ አባት የአባ መልአኩ ወልደ ሚካኤል መመረጥ የቀድሞው አድኃሪ ሥርዓት ተገዥች በመሆን ዓላማቸውን ለዘነጉ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ተግሣጽና ምክር ነው ። «ሥራህን አውቃለሁ ወይ አልሞቅ ወይ አልቀዘቀዘ ? እንዲሁ በመሀል ቤት ለብ ያለ ነውና» እንደ ተባለው ሁሉ በአፍአዊ አርአያነቸውና አለባበሳቸው መንፈሳዊያን ሲመስሉ በልቡናቸውና በተግባራቸው ሥጋውያን በመሆን የሥጋዊውንና የመንፈሳዊው ዓለማት ስደተኞች ለሆኑትም ሰነፎች ከፍተኛ ትምህርት ነው» ሰዎች ገጽን ያያሉ እግዚአብሔር ግን ልብን ይመለከታል» እንደ ተባለው የእግዚአብሔርን ቸርነትና ፍጥረቱንም የማይዘነጋ መሆኑን ስናስብ ለአምልኮቱ ምስጋና ማቅረብ ይገባናል ።

እነሆ የተመረጡት አባት በነበሩበት ሀገረ ስብከት የፈጸሙት ሐዋርያዊ ተግባር በግብር የተገለጸ በመሆኑ ለዚህ ከፍተኛ አባትነት በሥራው ለመመረጥ እንደበቁ ሁሉ በተሰጣቸው ልዩ የሥራ ዕድልና ትጋት የካህናትን ጉስቁልና የቤተ ክርስቲያንን ሐሜትና ነቀፋ የምእመናንንም መንፈሳዊ ችግር እንደሚያቃልሉ የሁላችን እምነትና ተስፋ ስለሆነ በአባታዊ ምክራቸውና በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ ልንተባበራቸው ይገባናል ። የቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆነ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በጸጋውና በረድኤቱ እንዳይለያቸው ፤ ሐዋርያዊ ተግባራቸውንም በአምላካዊ ቸርነቱ እንዲያቃናላቸው ያለማቋረጥ መጸለይ የእያንዳንዳችን ክርስቲያኖች ኃላፊነትና ተግባር ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኤጲስ ቆጶስነት ሥርዓተ ሢመት አፈጻጸም ፤

፩ሺ.፩፻፺፱ የ፲፬ ክፍላተ ሀገርና እንዲሁም የጥንታውያን ገዳማትና አድባራት ተወካዮች በተገኙበት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በዲሞክራሲ መንፈስ በተካሄደው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ምርጫ በዕጩነት ከቀረቡት ፰ ሊቃነ ጳጳሳትና ፫ አበው መነኰሳት መካከል አባ መልአኩ ወልደ ሚካኤል በሲዳሞ ሀገረ ስብከት የወላይታ አውራጃ ሐዋርያ በ፫፻፲፯ ድምፅ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የ፫ኛ ጊዜ ፓትርያርክነት መመረጣቸው ይታወሳል ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በመዐርገ ምንኵስና ደረጃ ያሉ እንደ መሆናቸው መጠን የፓትርያርክነቱን ሥልጣን ከመቀዳጀታቸው አስቀድሞ ሥርዓተ ኤጲስ ቆጶስነትን መፈጸም የቤተ ክርስቲያን ሕግ ስለሆነ ይኸው የኤጲስ ቆጶስነት ሥርዓተ ሢመት ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም እሑድ በመንበረ ጸባኦት ቅ/ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሞላቸዋል ።

የኤጲስ ቆጶስነት ሥርዓተሢመት የተፈጸመላቸው በብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተጠባባቂ ፓትርያርክ መሪነትና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት ሲሆን በዚሁ ስነ ሥርዓት ላይ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የአድባራት አለቆችና የገዳማት አበምኔቶች ፡ ካህናትና መዘምራን እንዲሁም በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ምእመናን ተገኝተዋል ።

በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፷፰ዓ.ም. ቅዳሜ ከቀትር በኋላ በ፲፩ ሰዓት ላይ በመንበረ ፓትርያርክ ቅ/ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በተጠባባቂው ፓትርያርክና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አማካይነት የጸሎተ አስኬማው ስነ ሥርዓት ተፈጽሞላቸዋል ።

ከቤተ ክህነት ጠ/ጽ/ቤት በወጣው ፕሮግራም መሠረት ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም በ፲፪ ሰዓት ከየአድባራቱ የተውጣጡ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት፤ እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፣ የአስመራጭ ኮሚቴ አባሎችና የመንግሥት ተወካዮች በመንበረ ጸባኦት ቅ/ሥላሴ ካቴድራል እንደ ተገኙ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ተጠባባቂ ፓትርያርክና ኤጲስ ቆጶስነት የሚሾሙት አቡነ ተክለ ሃይማኖት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ታጅበው ከቤተ ክርስቲያኑ ሲደርሱ ለ፫ ደቂቃ ያህል የደወል ድምፅ ተሰምቶአል ።

በዚህም ጊዜ ካህናቱና ዲያቆናት፡ «ብሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር» የሚለውን መዝሙረ ስብሐት እየዘመሩ ተቀብለዋቸዋል ።

ከዚያም ተጠባባቂው ፓትርያርክ ከተሿሚው ጋር ከቤተ መቅደሱ እንደ ደረሱ በ፲፪ ሰዓት ተኩል ላይ የጸሎተ ቅዳሴው ስነ ሥርዓት ተጀምሮ በተጠባባቂው ፓትርያርክ መሪነት፣ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት፡ በመካሄድ ላይ እንዳለ የኤጲስ ቆጶስነቱ የጸሎት ስነ ሥርዓት ተከናውኗል ።

በዚህ መሠረት ተጠባባቂው ፓትርያርክ በተሿሚው ኤጲስ ቆጶስ ላይ እጃቸውን ጭነው«ይደልዎ! ይደልዎ! ይደልዎ !» በማለት የተሿሚውን ኤጲስ ቆጶስ ስም ተክለሃይማኖት ብለው ሠይመዋቸዋል። ካህናቱና ምእመናኑም ይህንኑ ተቀብለው «ይደልዎ! ይደልዎ! ይደልዎ! » እያሉ በመንፈሳዊ ዝማሬ ደስታቸውን ገልጸዋል ።



www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኤጲስ ቆጶስነት ማዕርግ በተቀበሉበት ወቅት

www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኤጲስ ቆጶስነት ሥርዓተ ሢመት አፈጻጸም ፤

ቀጥሎም «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» የሚለው ምስባክ ከተሰበከ በኋላ ተጠባባቂው ፓትሪያርክ ከዮሐ. ወንጌል ከምዕራፍ ፲ ከቍጥር ፩ እስከ ፲፱ ያለውን ቃል ከአነበቡ በኋላ «ቸር እረኛ እኔ ነኝ» በሚል መነሻ ሰፋ ያለ ቃለ ምዕዳን አሰምተዋል ።

ከዚያም መዘምራኑ «እግዚአብሔር አምላክነ» የሚለውን መዝሙር ከዘመሩ በኋላ ተሿሚው ኤጲስ ቆጶስ ወንጌሉን ይዘው ከቅድስቱ ወደ መቅደሱ በመግባት በመንበሩ ቀኝ ቆሙ ፤ በዚህ ረገድ ጠቅላላ የጸሎተ ቅዳሴው ስነ ሥርዓት እንደ ተፈጸመ «ንፍሑ ቀርነ በዕለተ ሠርቅ በእምርት ዕለት በዓልነ፥እስመ ሥርዓቱ ለእስራኤል ውእቱ» የሚለው ምስባክ ከተሰበከ በኋላ ተጠባባቂው ፓትሪያርክ ከዮሐንስ ወንጌል ከምዕራፍ ፳ ከቍጥር ፲፱ እስከ ፳፫ ያለውን አንብበው ሲጨርሱ ለተሿሚው ኤጲስ ቆጶስ ሥርዓተ ቅብዑን ፈጽመውላቸዋል ። ከዚሁ በማያያዝ አርዌ ብርቱን ለተሿሚው ኤጲስ ቆጶስ ከሰጡ በኋላ በዚሁ ጊዜ የሚከተለውን ቃለ ምዕዳን አሰምተዋል ።

«ይህ አርዌ ብርት /በትረሃይማኖት/ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖትና ለሕዝብ የሚያደርሱበት ከአጋንንትና ከሌሎችም መናፍቃን የሚከላከሉበት ምልክት ነው ።

ስለዚህ ይኸ ሲሰጥ ሊያጌጡበት አይደለም ፤ ሥራ ሊሠሩበት ነው እስካሁን ድረስ ራስዎ በሠሩት ኃጢአት ነው ይፈረድብዎ የነበረው ፤ አሁን ግን የመላውን የኢትዮጵያን ክርስቲያን ኃጢአት ሁሉ በርስዎ በራስዎ ላይ ተሸክመውታል፤ሊያንቀላፉም ፤ችላ ሊሉም አይገባዎትም፤ካሉ በኋላ ወደ ሕዝበ ክርስቲያኑ መለስ ብለው ብንሰማቸውና ቃላቸውን ብናከብር ነው እንጂ እንዲያው ይደልዎ ! ይደልዎ ! ብቻ ብለን አጨብጭበን ብንሄድ የክርስቲያንነት ሥራ አይደለም፥ቃላቸውን አለመስማት እሳቸውን መናቅ አይደለም፥መላውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መናቅ ነው ። እሳቸው አንድ የወደቁ መነኰሴ ናቸው፥ ወደውም አይደለም፥ የመጡ፥ እግዚአብሔር በቸርነቱ እንዲረዳቸው ፤ እየሰማችሁ የጠመመውን እንዲያቃኑ ያጠረውን እንዲያስረዝሙ፥ የፈረሰውን እንዲያሳንጹ ፤ ሁላችንም አንድ ልብ ሁነን ስንረዳ ነው እንጂ ፓትሪያርክ ተሾመዋል ብቻ ብለን ብናወራ አይሆንምና እግዚአብሔር መዋዕለ ሢመታቸውን የተባረከ የተቀደሰ ያድርግልን፥ ይህ አርዌ ብርት /በትረ ሃይማኖት/ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብና ሠራዊት የሚጠበቅበት ምልክት ነውና እግዚአብሔር በዚህ በትረ ሃይማኖት ሕዝቡን የሚገሥጹ፥ የሚመክሩ መርተው መንግሥተ ሰማያትን የሚያወርሱ እንዲያደርግልዎ ይህን የሃይማኖት በትር እሰጥዎታለሁ ። በማለት አርዌ ብርቱን ለተሿሚው ኤጲስ ቆጶስ ከሰጡ ቸው በኋላ በመንበረ ጸባኦት ቅ/ሥላሴ ካቴድራል የተካሄደው የኤጲስ ቆጶስነት ሥርዓተ ሢመት ተፈጽሞ በተጠባባቂው ፓትሪያርክ ቃለ ቡራኬ ሠርሆተ ሕዝብ ከሆነ በኋላ ተሿሚው ኤጲስ ቆጶስ በመጡበት አኳኋን ወደ መንበረ ፓትርያርኩ ተመለሱ፤ በዚሁ ዕለት በመንበረ ፓትርያርኩ ልዩ ልዩ የደስታ መዝሙሮች ተዘምረዋል፥ ከሊቃውንትም ልዩ ልዩ ቅኔዎችና ድርሰቶች ተሰምተዋል ።

በመጨረሻ የሪሴብሽን ግብዣ ተደርጎ ጠቅላላ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አጭር ታሪክ

«የክርስትናን ሃይማኖት በመቀበል በአረማውያን መካከል በዙር ለሆነውና ወንጌል መንግሥት ለተሰ በከለት ሕዝብ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደእግዚአብ ሔር ትዘረጋለች ተብሎ የተነገረው ትንቢት ተፈ ጸመላት » ። የሚል ግልጽ የታሪክ ምስክርነት አለ። ይህም ምስክርነት « ከክርስቶስ እስከ ቈስጠንጢ ኖስ » በሚል ርእስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት እየተባለ የሚጠራው አውሳብዮስ ዘቂሣርያ የጻፈው ነው ።

(ገጽ ፳፯)

የክርስትና ሃይማኖት ወደኢትዮጵያ መግባት የጀመረው ገና በአንደኛው ምእት ዓመት ከኢትዮጵያ ዊው ጃንደረባ ታሪክ ሲታይ ዘመነ ሐዋርያት ከመፈ ጸሙ በፊት መሆኑ የማያከራክር ዓለም አቀፍ ሐቅ ነው (የሐዋ ፰ ፡ ፳፯ — ፴፱) ።

ይሁን እንጂ ክርስትና በኢትዮጵያ መንግሥ ታዊ ሃይማኖት ሆኖ በይፋ መሰበክና መስፋፋት የቻ ለው ከ፬ኛው ምእት ዓመት አንሥቶ ከሣቴ ብርሃን ዘኢትዮጵያ በተሰኘው አባ ሰላማ (ፍሬ ምናጦስ) አማካይነት ነው፤እንደገና አምስተኛው ምእት ዓመት በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጸም ዘጠኙ ቅዱሳን ከመካከ ለኛው (ቅርብ) ምሥራቅ ወደኢትዮጵያ መጥተው በሰሜኑ ክፍል ሥርዓተ ምንኵስናን አስተምረው ገዳማትን መመሥረት ጀመሩ ። እንዲሁም ከ፯ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ አዲስ የዜማ ትምህርትና አዲስ ስነ ጽሑፍ ማንበብ የቀጠለበት ክፍለ ዘመን ስለ ነበር በዚሁ ጊዜ ነው ታላቁ ስመጥሩ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅ/ያሬድ የመጻሕፍት ብሉያትንና ሐዲሳትን ትርጉም በመተንተን የመዝገበ ድጓውን ድርሰት ያበረከተ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ ያን ከጥንታዊት የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር የሥርዓተ እምነት አንድነትና የእኅትማማችነት ኅብረት ስለነበራት ግብጻውያን ጳጳሳት ሥልጣነ ክህነት በመስጠት ብቻ ተወስነው፥ የቀረው የአስተ ዳደሩና የውስጥ አመራሩ ይዞታ ግን በኢትዮጵያው ያን ሊቃውንት ይካሄድ እንደነበር ታሪክ የማይክ ደው ሐቅ ነው ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን በጥንታዊ ሥርዓት ኑሮ ፣ በሥርዓተ ትምህርትና በባህል ራሱን የቻለ አቋም የነበራትና ያላት መሆኑ ትናንትም ዛሬም በታሪክ የተመሰከረ ነው ።

በተለይ ከ፲፪ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገትና መስፋፋት ከከፍተኛ ደረጃ ደርሶ እንደነበረ ከደንጊያዎች ተፈልፍለው የተሠ ሩት የላሊበላ ሕንጻዎች ዘለዓለማዊ ምስክርነት ይሰጣሉ ። ከዚሁ በማያያዝ ፲፫ኛውና ፲፬ኛው ምእት ዓመታት በወንጌል ስብከት መስፋፋት ረገድ የታላላቅ ደራስያንና ሰባክያን ትንሣኤ የታየበት ዐረፍተ ዘመን በመሆኑ ዘመነ ተሐድሶ እንደነበር በታሪክ ተጽፎአል ።

እንዲሁም ከ፲፯ኛው ምእት ዓመት ፍጻሜ ላይ ይጀምርና (በተለይ በጎንደር ዘመነ መንግሥት ማለት ነው) በግእዝ ብቻ ሳይሆን በአማርኛም ጭምር ስነ ጽሑፍ እያበበ የቅኔ ማዕበልና ሞገድ የተነሣበትና አያሌ ስመጥሩ የቅኔና የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቃ ውንት የበዙበት ጊዜ ሲሆን የሥዕልና የቅርጻ ቅርጽ ሙያም የተስፋፋበት ዘመን ነበር ። የቤተ ክርስቲያ ኒቱ የታሪክ ጕዞ በዚህ ዓይነት ቀጥሎ ከ፲፱ኛው ምእት ዓመት መጀመሪያ ላይ ሲደርስ አዲስ ምራፍ መክፈት ይጀምራል።ይኸውም ቀደም ብሎ በግብጻውያን ጳጳሳት ይዞታ ሆኖ የቆየው፤ የጵጵስና ማዕርግ ለኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ይሰጥ የሚ ለው ቀጥተኛ ጥያቄ ነው ።


ይህም ጥያቄ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንትና ምእመናን ሲጠና ቆይቶ ኢትዮጵያውያን ምሁራን እስከፓትርያርክነት ያለውን ማዕርገ ሢመት ከመጐ ናጸፍ የሚያግዳቸው ምንም ምክንያት ባለመኖሩ በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም. ዐራት ኢትዮጵያውያን ተመርጠው ጵጵስና ተሾሙ ። በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም. የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ጳጳስ ወደሊቀ ጵጵስና ከፍ አለ ። ያም ሊቀ ጵጵስና በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. ወደፓትርያርክ ነት ደረጃ ለመድረስ ስለበቃ የመንፈሳዊ ማዕርጋት ሁሉ መደምደሚያ ሆነ ። በዚህ ዓይነት ባለፉት ፲፯



www.ethiopianorthodox.org

ዓመታት ውስጥ ሁለት ኢትዮጵያውያን ፓትርያርኮች የተሾሙ ሲሆን የአሁኑ ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፫ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ መሆናቸው ነው ።

በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያኒቱ የ፩ሺ፮፻ ዘመን ታሪክ ያላት ሲሆን እስካሁን የታነጹት አብያተ ክር



አዲሱ የጥንታዊት አኵስም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን

ስቲያናት ገዳማትና አድባራት ፣ ገጠሮችም ጭምር ፲፫ሺህ ያህል ሲሆኑ ከ፳፫ ሚሊዮን ሕዝብ መካከል ከ፲፫-፲፯ ሚሊዮን ተከታዮች ያሏት መሆኑ ይታመናል

## ፪ ትምህርትና ስብከት

ከጥንት ሲያያዝ በመጣው ወግና ሥርዓት የቤተ ክርስቲያኒቱ ነባር የትምህርት ዓይነቶች ፤

ሀ/ መሠረተ ትምህርት ፣
ለ/ ሥነ ጽሑፍ ፤
ሐ/ ፀዋትወ ዜማ ፣
መ/ ትርጓሜ መጻሕፍት ፣
ሠ/ ቅኔና የሕግ ትምህርት ፣
ረ/ የቊጥር ትምህርት (አቡሻኸር)
ሰ/ የቁም ጽሕፈት የሥዕልና ቅርጻቅርጽ ሙያ

ሲሆኑ በእነዚህም የትምህርት ዓይነቶች የተገኘው የዕውቀት ፍሬ ቀላል አልነበረም ።

በመሠረተ ትምህርት መሃይምነትን ስታስወግድ ኑራለች ።

በፀዋትወ ዜማ ትምህርት—አያሌ መዘምራንን በማፍራትና መንፈሳዊ ዝማሬን በመፍጠር እግዚአብሔርን በመዝሙር ለማመስገንና በመዝሙር ለመጸለይ በቅታለች ።

በትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት ፣ የብሉይንና የሐዲስን ምሥጢር በግልጽ ታስረዳበታለች ። በቅኔ ትምህርት የተማሪዎችን አእምሮ በማዳበር የሥነ ጽሑፍ ባሕርይ ውበት እንዲኖረው ታደርጋለች ፣ በሕገ ትምህርት ጊዜው በሚፈቅደው መጠን ፍትሕንና ርትዕን ለኅብረተ ሰቡ ስታስተምርበት ኑራለች ። በሥዕልና ቅርጻቅርጽ ትምህርት ፣የእደ ጥበብን ሙያ ለየትውልዱ ከማስተዋወቋም በላይ አብያተ ክርስቲያናትን በተለያየ የሥዕልና ቅርጻቅርጽ ውበት ስታስጌጥበት ኑራለች ።

አንድ ተማሪ ከቤተ ሰቡ ተለይቶ ወደፈለገው አገር በመሄድ በአካባቢው ሕዝብ ርዳታ መማርና ሕዝቡም ማንኛውንም ዓይነት ተማሪ እንደራሱ ልጅ በመቍጠር ማስተማር የኅብረተ ሰቡ ጥንታዊና አሁንም ፈጽሞ ያልተረሳ ባህልና ሥርዓት ስለሆነ ትምህርቱን ለማዳረስ ችግር አልነበረም ።

ይህም የትምህርት ዓይነት እስከአሁን ድረስ ለአገሪቱ የታሪክ ምንጭ ፤ እንዲሁም እየተሻሻለ ለሚሄደው ሥርዓተ ትምህርት ጽኑዕ መሠረት በመሆን በአገልግሎት ላይ ይገኛል ።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት ዓይነትና ይዞታ በአሁኑ ጊዜ ያሉበትን ጊዜና የጊዜውን ጠባይ አለ



www.ethiopianorthodox.org

ማወቅ ቤተ ክርስቲያንን ከአደገኛ ሁኔታ ላይ ሊጥል ይችላል ፤ ምክንያቱም ጠባዩና ቋንቋው በማይታወቅ ዓለም ላይ በአስተማሪነት መሰለፍ በቋንቋ አለመግባባት ምክንያት ሊገጥም የሚችለውን ችግር ለማስወገድ ብዙ ሙከራ አድርጋለች ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ትምህርት መሠረት በማድረግ በዚያ መሠረትንት ላይ ተማሪዎቿ ዘመናዊውንም ትምህርት እንዲከታተሉ ማድረግ ከጀመረች ቆይታለች። ሕጻናት ወደ ዘመናዊ ት/ቤት ከመግባታቸው በፊት በብዙ ቦታ በየመንደሩ «መሠረተ ትምህርት » ይማራሉ ፤ እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች በተቻለ መጠን በራስዋ ኃላፊነት የሚካሄዱ ት/ቤቶችን በመክፈት መንፈሳዊውንና ዘመናዊውን ትምህርት ታስተምራለች ።

ከዚህም በላይ ካህናትን በኮርስ በማሠልጠን የጊዜውን ዓለም ችግርና ፈተና የሚያውቁ ምሁራን ሰባክያንን ማሠማራት ጀምራለች ፤ የነበረውና ያለው መንፈሳዊ ኮሌጅም ከድሮው በበለጠ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችልበት መንገድ ተጠንቷል ።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ከውጭ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ባላት ክርስቲያናዊ ግንኙነት በአንዳንድ አገሮች የውስጥም ሆነ የውጭ ትምህርታዊ ርዳታ ተቀብላለች ። የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ለብዙዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ደቀ መዛሙርት የነጻ ትምህርት ዕድል በመስጠት ከፍ ያለ አገልግሎት በማበርከት ላይ ሲገኙ የጀርመን ሕዝበ ክርስቲያን ደግሞ «ኬ-ኤን-ኤች» K.N.H. ና ብሬድ ፎር ዘወርልድ (Bread for the world) በተባሉት ድርጅቶች አማካይነት በአገር ውስጥ በዛ ያሉ ትምህርት ቤቶችን በመክፈት ተማሪዎች መንፈሳዊውንና ዘመናዊውን ትምህርት እንዲከታተሉ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያኒቱም ሆነ ለኅብረተሰቡ ከፍ ያለ ተራድኦ በማድረግ ላይ ነው ። ተማሪዎቹ የሚማሩት ከላይ በተጠቀሰው ድርጅት በሚላክ ላቸው ገንዘብ በእስኮላርሽፕ መልክ ሲሆን የየት/ቤቶቹ አስተዳደርም ሆነ ትምህርት የሚመራው በቤተ ክርስቲያኒቱ ኃላፊነት በቦርድ ስለሆነ የውጭ ሥልጣንና ተጽዕኖ የሌለበት ንጹሕ ርዳታ በመሆኑ በሕዝብ ዘንድ ያለው ተቀባይነትና ተወዳጅነት ቀላል አይደለም ። ቤተ ክርስቲያኒቱ በምታደርገው ትምህርታዊ እድገትና መሻሻል የተባበሯትን እነዚህንና ሌሎችንም የውጭ አብያተ ክርስቲያናት ከልብ ታመሰግናለች ።

## የቤተ ክርስቲያኒቱ የስብከት ስልትና ይዞታ ባለፈው ጊዜ

ቤተ ክርስቲያኒቱ የሃይማኖት ትምህርት እንቅስቃሴዋን በማስፋፋት በሚሊዮን የሚቈጠር ተከታይ ለመፍጠር የበቃችው በአጭሩ በ፩ ዋና ዋና መንገዶች ነበር ፤ ይኸውም ፤

ሀ/ ለምእመናኑ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ወንጌልን በመስበክ ፤

ለ/ ለሕፃናቱ በየመንደሩ መሠረተ ትምህርት በምትሰጥበት ጊዜ በተጨማሪ ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን በመስጠት ፤

ሐ/ ለክርስቲያኑ ቤተ ሰብእ ቀሳውስትን በነፍስ አባትንት (በሞግዚትንት) በመመደብ ፤

መ/ በይበልጥ ትዳርና ቤተ ሰብእ የሌላቸውን መናኝ ሰባክያን የእግዚአብሔር ቃል ወደ አልተዳረሰበት ኅብረተ ሰብእ በመላክ ያላመነውን ወገን በማሳመን ነው ።

### ቤተ ክርስቲያኒቱ ያላትና ሊኖራት የሚገባ የስብከት ስልትና ይዞታ በአሁኑ ጊዜ፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የክርስትናን ትምህርት ለማስፋፋትም ሆነ በክርስትና እምነት ያሉትን ምእመናን ለመጠበቅ የምትጠብቅበት እስከ አሁን የነበረውና ያለው የስብከት ዘዴ (ስልት) ወደፊት የ ሚቀጥል ቢሆንም እንደጊዜው ሁኔታ መሻሻልና መታደስ ይኖርበታል ። ይህኑ በመገንዘብ ቤተ ክርስቲያኒቱ የተማሩና በኮርስ የሠለጠኑ የወንጌል መምህራንን በየክፍለ ሀገሩ በማሰራጨት ላይ ከመሆንዋም በላይ በሚሊዮን ለሚቈጠሩ አድማጮች በኢትዮጵያና በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያዎች አማካይነት በ፬ ታላላቅ ብሔራዊ ቋንቋዎች ( በግእዝ በአማርኛ ፡ ትግሪኛ፡ኦሮሙኛ) ቃለ ወንጌል ታሰማለች ። ከዚህም ጋር በሳምንትና በወር እየታተሙ የሚወጡ ሁለት ጋዜጦች አሉዋት ። በሚያስፈልግበትም ጊዜ ሁሉ ልዩ ልዩ መጽሔቶችና መጻሕፍትን ታሳትማለች ።

ቤተ ክርስቲያኒቱ በዚህ አሁን ባለችበት ሐያኛው ክፍለ ዘመን በመካሔድ ላይ ካለው የአስተዳደር ተሐድሶ ባገኛችው መንፈሳዊ ንቅሐተ ኅሊና ለአዲሱ ትውልድ የክርስቶስን ወንጌል ለማዳረስ በአ



www.ethiopianorthodox.org

ዲስ መንፈስ የተንሣሣበት ጊዜ ነው ። ባጠቃላይ ወደፊት የምትከተለው ዓላማ ፣

፩/ በየጊዜው በሚለዋወጠው አዲስ ዓለም ፊት የማይለወጠውን ቃለ እግዚአብሔር በአዲስ ቋንቋ አቀራረብ ለመስበክ መቻል፣

፪/ ከቃል ስብከት በበለጠ ሁኔታ የእምነትን ኑሮ መልካምነት በራሱ ኑሮ ምሳሌነት መግለጥ ፤

፫/ የግዙፍ ዓለም ምቾትና ጸሎት ሊያረካው ባልቻለው ዘመናዊ ኅብረተሰብ ፊት ፍቅ ርና መንፈሳዊ ደስታ የተመላበት ክርስቲ ያናዊ ኑሮ በመኖር በአርአያነት ወደእም ምነትና ክርስቲያናዊ ሕይወት መሳብ

፬/ ዓላማ ፣ ተስፋና ትዕግሥት ያለው ሐዋ ርያ በመሆን በዓለም ፊት መሠለፍ ነው ።

ለዚህም ሁሉ ተግባር መንፈሳዊ ኃይልን ለማ ግኘት እጆቿን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋ ለች ።



www.ethiopianorthodox.org

የ፫ኛው ፓትርያርክ በዓለ ሢመት ።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምግባረ ሠናይ

ከአሱባለው ወ/ ሥላሴ ፤

ምግባረ ሠናይ ማለት፣ በጎ ሥራ ማለት ነው ። የተራቡትን ማብላት፣ የታረዙትን ማልበስ ፣ የታመሙትን መጠየቅና ማሳከም ፣ በጎ ሥራዎች ናቸው። ከዚህ በቀር ሰውን ከድንቁርና ለማላቀቅ ማስተማር ፣ ሲጨነቅ ማጽናናት በጎ ሥራ ነው ። በጠቅላላው ሰውን ከችግሩ ለማዳን የሚሰጠው የቁሳቁስና የመንፈስ ርዳታ ሁሉ በጎ ሥራ ነው ። ክርስቶስ በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ ሰዎች በጎ ሥራ እንዲሠሩ አስተምሯል ፣ እሱም ራሱ በጎ ሥራዎችን ሠርቷል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ምሳሌ በማድረግ በጎ ሥራን ስታስተምር ኖራለች ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ውስጥ ተቀዳሚነት የሚሰጡት ለበጎ ሥራ ነው ፣ ሊቁም ሆነ ተራ ሐዋርያ ሲያስተምር ቆይቶ በመጨረሻ ስለ በጎ ሥራ ሳይጠቅስ አያልፍም ፣ በተለይ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ«እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ፣ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ። ተርቤ አበልታችሁኛልና ፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና ፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና ፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና . . . እውነት እላችኋለሁ ፤ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ከወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስለ አደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል ። . . . እናንተ ርጉማን ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ሂዱ ፣ ተርቤ አላበላችሁኝምና ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና . . . »/ ማቴ ፳፭፣ ፴፫—፵፮/ የሚለውን ሲያስተምሩ ኖረዋል ። እንዲያውም «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ» እንዲሁም ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው ። የሚለው የሐዋርያው ያዕቆብ መልእክት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ትምህርት መሠረት ነው ሲሉ ዶክተር ኤፍሬም ይስሐቅ የተናገሩትን ቃል ማስታወስ ይጠቅማል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰው ልጆች መካከል ስላለው ግንኙነት ያለው አስተያየትና እምነት የተመሠረተው በቤተ ክርስቲያን የበጎ ሥራ ትምህርት ላይ ነው ።

አንዳንድ ጊዜ በሰው መካከል ጠብ ተነሥቶ እስከ ነፍስ ግዳይ እንኳ ቢደርስ ነፍስ ገዳዩ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ደመኞቹ እንዳይበቀሉትና እንዲታረቁት ቤተ ክርስቲያንን ከተማጠነ ሁለቱን ደመኞች በማስታረቅ ሰላምን ታወርድላቸዋለች ።

ከዚህም በስተቀር ሕዝቡ በማኅበር ፣ በሰንበቴና በልዩ ልዩ ሰበካ መገናኛዎች በእርጅናና በበሽታ ምክንያት ጉልበታቸው ደክሞ ሠርተው ራሳቸውን ለመርዳት ለማይችሉት ሰዎች ምግብና ልብስ በመስጠት ይረዳል ። በአንዳንድ ክፍለ ሀገር መንገደኛ ለመርዳት በማሰብ ሕዝቡ በመንገድ ዳር ማኅበር ይጠጣል ።

በአዲስ አበባና በሌሎች በብዙ የሚቈጠሩትን ደካሞች ፣ ዘመዶቻቸው ሊያሳድጓቸው ያልቻሉትን ሕፃናትና እንዲሁም በሥራ እጦት ምክንያት የዕለት ችግራቸውን ለማስወገድ የማይችሉትን ሰዎች ሕዝቡ በምግብና በልብስ እንዲሁም በገንዘብ ይረዳል ። በዚህ ምክንያት ማንም ችግረኛ መሄጃ ሲያጣ ሕዝበ ክርስቲያኑ እንደሚረዳው ስለሚተማመን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ይጠጋል ።

የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለመከታተል ሲፈልጉ ከተወለዱበት ሀገር ከወላጆቻቸውና ከዘመዶቻቸው ተለይተው ወደ ሌላ ሀገር ይሄዳሉ ። የሚሄዱበት ሀገር ሕዝብም ያለ ምንም ቅሬታ ተቀብሎ ያስተናግዳቸዋል፣ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ መጡበት ሀገር እስ ከተመለሱ ድረስ እንደ ባዕድ ሳይመለከታቸው ሁለት ሦስቱን እየተካፈለ በየቀኑ ለምግባቸው የሚያስፈልጋቸውን እንጀራም ሆነ ጥሬ እየሰጣቸው ሲያስተምራቸው ኖሯል ፣ አሁንም በማስተማር ላይ ይገኛል፣በዚህ ዓይነት የተማሩት ኢትዮጵያውያን በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ናቸው ። ከኢትዮጵያ በቀር በዓለም ውስጥ ተማሪዎችን በዚህ ዓይነት መንገድ እየረዳ የሚያስተምር ሕዝብ ያለ አይመስልም ።



www.ethiopianorthodox.org

## የኢትጵዮያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምግባረ ሠናይ ።


የኢትዮጵያ ሕዝብ በእንግዳ ተቀባይነት በማ
ንም ዘንድ የታወቀ ነው ፤ አንድ ሰው ከሀገሩ ያለም
ንም ስንቅ ወጥቶ ሲሄድ ውሎ ማታ ሲመሽበት ያለ
ምንም ስጋት ከደረሰበት መንደር አንዱን ቤት
መርጦ የእግዚአብሔር እንግዳ ነኝና አሳድሩኝ ቢል
ባለቤቱ በመልካምተቀብሎ ጥሩ አድርጎ አስተና
ግዶከአሳደረው በኋላ ጧት ይሸኘዋል ። ይህ የሕዝቡ
የደግነት ጠባይ የመነጨው ቤተ ክርስቲያን ከምታ
ስተምረው ትምህርት መሆኑ አያጠራጥርም ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊውን ሥር
ዓት በዘመናዊ መንገድ በሥራ ላይ ለማዋል ትጥ
ራለች፤ እናት አባት የሌላቸውንና እንዲሁም ወላ
ጆቻቸው በድህነት ምክንያት ሊያስተምሯቸው ያል
ቻሉትን በብዙ መቶ የሚቈጠሩ ወጣቶችን ሰብስባ
በቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ፥ በሐረር መንፈሳዊ
ትምህርት ቤት፥በበኣታ ገዳምና በልዩ ልዩ ቦታዎች
አስፈላጊውን እንክብካቤ እያደረገች በማስተማር
ለሀገር አገልግሎት አበርክታለች ። ዛሬም በአዲስ
አበባ ፥ በየክፍለ ሀገሩና በየገዳማቱ በአዳሪነትና ገን
ዘብ በመረዳት የምታስተምራቸው ተማሪዎች ብዛት
ከ፪፻ በላይ ነው ።

ከዚህም በቀር ቤተ ክርስቲያን በዕድሜ
ያረጁትንና በሕመም ምክንያት በሥራ ራሳቸውን
ለመርዳት ያልቻሉትን ድኩማን ትረዳለች ። በደብረ
ሊባኖስ፥ በበኣታ በዋልድባና በመሳሰሉት ገዳማት
ብዙ ችግረኞችን ትረዳለች ።

ሆኖም እስካሁን ሕዝቡ ይሰጥ የነበረው ርዳታ
ዕለታዊ ችግርን ከማቃለል አልፎ ዘላቂ መፍትሔ
አልሰጠም ።

ስለዚህ ወደፊት የሕዝቡን የገንዘብ ኃይል በማ
ስተባበርና በየሰበካው ድርጅት ለማቋቋም ገንዘብ
እያዋጣ በልዩ ልዩ ምክንያት ጉልበታቸው የደከ
መውን ሲጦሩና አቅማቸው ለሚፈቅድላቸው ደግሞ
ልዩ ልዩ የእጅ ሥራዎችን አስተምሮ እየሠሩ ራሳ



በኮልፌ ቤተ ክ፡ ያሉትን ሕፃናት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ተጠባባቂ
ፓትርያርክ ሲጎበኙ

ቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል ።
የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅቶችንና አዳሪ ትምህርት
ቤቶችን አመች በሆኑ ቦታዎች ለማስፋፋት ታቅ
ዷል ።



www.ethiopianorthodox.org

# የውጭ ግንኙነት (ኤኩሜኒካል)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአፍሪካ ከሚገኙ ቀደምት አብያተ ክርስቲያናት አንዷና ዝነኛዋ ናት ። በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ ኢትዮጵያን ስታስጠራ ኑራለች ። ግንኙነቷም ከአፍሪቃ ብቻ ሳይሆን ጥንትም ሆነ ዛሬ ከመላው ዓለም ጋር ነው ።

ይህች ቤተ ክርስቲያናችን በዓለም ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት መካከል በተለይ ከአምስቱ የመካከለኛው የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ፤ ወይም ቀዳምያን በመባል ከታወቁት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ናት ። እንዲሁም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች አባል ስትሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናትም ዓላማቸው ሁሉ ክርስቲያናዊ አገልግሎታቸውን በአንድነት ለሰው ልጅ ማበርከት በመሆኑ ይህንኑም ከፍጻሜ በማድረስ ጥንታዊ ዓለም አቀፍ ግንኙነቷን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻለች እንደሄደች ከዚህ ቀጥለን እንገልጻለን ።

# ከግብጽ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ

## ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላት ግንኙነት

የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቀድሞ ሞግዚት ሆና መቆየቷ ይታወቃል ። በዚህም ረጅም ዘመን ውስጥ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ከመካከላቸው ጳጳስ እንዳይመረጡና እንዳይሾም "በኒቂያ ጉባኤ" ተከልክሏል የተባለውን ሥርዋጻዊ ጥቅስ ምክንያት በማድረግ ሊሠሩ የሚገባቸው እንደስብከተ ወንጌልና እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የመሳሰሉት ዓበይት ጉዳዮች ፤ ለ፩ሺ፮፻ ዓመታት ያህል ተጎትተው ቆይተዋል ። እንዲያውም በኢየሩሳሌም ያለውን የኢትዮጵያ ገዳም አቡነ ማቴዎስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የነበሩ ግብጻዊ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሰጥተዋል ። በዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጻውያን በቋንቋ ስለማይግባቡ ፤ ግብጻውያንም የኢትዮጵያን ቋንቋዎች ባለማወቃቸው ፤ ለሥራው መስፋፋት ችግር ገጥሞአቸው እንደነበር ሥራቸው ይመሰክራል ።

በ፲፩ኛው መቶ ዘመን የነገደ ዘጌው ንጉሥ ሐርቤ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጳጳስ እንዲሾምለት የግብጽን ቤተ ክርስቲያን ቢጠይቅ ሳይፈቅድለት ቀረ ። በ፲፱ኛውም ክፍለ ዘመን አፄ ቴዎድሮስም አባ ሰላማ የተባለው ግብጻዊ ጳጳስ ቤተ ክርስቲያኒቱን ባለመርዳቱ የኢትዮጵያና የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት በደንብ እንዲመረመርና እንዲጠና አድርገው ነበር ። እንዲያውም በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት ግብጻውያን ጳጳሳት ባለመምጣታቸው የኢትዮጵያ ሊቃውንት ተሰብስበው አቡነ ተክለ ሃይማኖትን መርጠው ሾመዋል ። አጼ ዮሐንስም በ፲፰፻፸፬ ዓ/ም ይህን መነሻ በማድረግ ጳጳሳትን ለመሾም ቢወስኑ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የአጼ ዮሐንስን አሳብ ተቃውማ አራት ግብጻውያን ጳጳሳትን ሾማ ላከች ።

በጊዜውም ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ጳጳስ እንዲሾሙላቸው ከመጠየቅ የተቆጠቡበት ጊዜ አልነበረም ። ግብጻውያን ግን ጥያቄውን ለመቀበል ከቶ ፈቃደኛ አልነበሩም እንደየሙያው ኢትዮጵያውያን በገጠማቸው ችግር ምክንያት የራሳቸውን ጳጳስ ስለሾሙ ግብጻውያን ከውግዘትም ደረጃ ደርሰው ነበር ። ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ስትወረር የነበሩት ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ ሸሽተው ከሄዱ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ የማይመለሱ መሆኑን አረጋግጠው ላኩ ስለዚህም ከኢትዮጵያውያን ጳጳሳት መካከል አንዱን መርጠው ለመሾም ሊቃውንቱ ተሰብስበው መክረው አቡነ አብርሃም በሊቀ ጳጳስነት ተሾሙ ። ኢትዮጵያውያን ይህን አድራጎት መፈጸማቸውን የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ስትሰማ አቡነ አብርሃምን አወገዘች ። የውግዘቱ ደብዳቤ ግን ወደ ኢትዮጵያ ሳይላክ ከዚያው ቀየ ። አቡነ አብርሃም በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም ስለሞቱ ፴፪ ሊቃውንት ተሰብስበው አቡነ ዮሐንስን ለሊቀ ጳጳስነት መርጠው መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ/ም ተሾሙ እርሳቸውም ጳጳሳትንና አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሾሙ ።

ኢትዮጵያ ነጻነቷን ስታገኝ አቡነ ዮሐንስ ግብጻዊ ፓትርያርክ ከግብጽ ቤተክርስቲያን ጋር ተቋርጦ የነበረው ግንኙነት እንዲቀጥል መልእክ



www.ethiopianorthodox.org

## የውጭ ግንኙነት

ተኛ ወደ አዲስ አበባ ላኩ ፤ በመልእክቱም መሠረት ከግንቦት ፴ እስከ ሰኔ ፲፫ ቀን ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ጉባኤ ተደርጎ የግብጽ ቤት ክርስቲያን ያወገዘችውን እንድታነሣ ንግግር ከተደረገበት በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን አስተያየት ከግብጽ የመጡት ፫ ሰዎች ይዘው ሄዱ ።

በዚህም ሁኔታ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ግዝቱን በከፊል ፈታች ነገር ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በጉዳዩ በጣም ስላዘነችበት በአስቸኳይ ከራሷ ሊቃውንት ሊቀ ጳጳስ ለመምረጥ እንድትችል ያለዚያ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ስለጠየቀች አቡነ ቄርሎስ በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ከኢትዮጵያ እንዲሄዱ ፤ ወዲያው መልክተኞች ወደ ካይሮ ተልከው በጉዳዩ በሰፊው ከተወያዩበት በኋላ ፭ መነኰሳት ወደካይሮ ለመሾም ሄዱ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን አንድ ውል አዘጋጅታ « የኢትዮጵያው ሊቀጳጳስ በበታቹ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት አይሾምም » የሚል በመሆኑ በዚህ የጭቆና ውል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለአልተስማማች ለሹመቱ የሄዱት ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ መጡ ፤ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀችውን ውል ሽራ ኢትዮጵያውያኑን ለመሾም በመስማማቷ በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆኑ እርሳቸውም ፭ ጳጳሳት ሾሙ ፤ በዚህም የጭቆናው ቀንበር ቀለል አለ ።

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የፓትርያርክነት ማዕረግ የምታገኝበት ሁኔታ ውይይት ቀጠለ ፤ አከራካሪ የሆነው ውስጥ ለኢትዮጵያዊው ፓትርያርክ የሚሰጠው ስያሜ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ስለሚሾማቸው ሊቃነ ጳጳሳት ሁኔታ ነበር፤ አሁንም በከፍተኛ ትግል ከአንድ ስምምነት ስለተደረሰ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ወደ ካይሮ ሄደው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ ።

የእግዚአብሔር ቸርነት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ አድሮ ከነበረባት ጭቆና ተላቀቀች ከዚህ በላይ የተገለጸው ትንሣኤ መጽሔት ቍጥር ፪ ላይ በሚቼ መላከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ ተዘጋጅቶ የተገኘ ነው፤ ከዚያም ወዲህ የወረዱት ፓትርያርክ በኢትዮጵያ መሬት የፓትርያርክነቱን ሹመት በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ተሾሙ፤ በአሁኑ ጊዜ ያ ሁሉ የነበረው ችግር ፈጽሞ ተወግዶ ሁለቱም እትማማች አብያተ ክርስቲያናት የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት አባላት ከመሆናቸውም በላይ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ግንኙነት በማድረግ በኢትዮጵያ ገዳም የሚያገለግሉ አንዲት ግብጻዊት ሲስተር ተልከው ለ፫ ዓመት ሰበታ በሚገኘው በቤተ ደናግል ጠባባት ገዳም በመምህርነት አገልግዋል፤ እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ ፳ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት በግብፅ በመከታተል ላይ ይገኛሉ ። በዚህ ዓይነት ትብብር ላይ በመሆናቸው ፈጣሪን ሊያመሰግኑት ይገባል ።

# የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት

## ስብሰባ በአዲስ አበባ

አዲስ አበባ ፤ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባኤ እንዲደረግ የቤተ ክርስቲያኒቱ ምኞት ነበር ሆኖም በልዩ ልዩ ምክንያት ምኞቷ ሳይፈጸም ቆይቶ የእግዚአብሔር ቀኑ ሲደርስ ከጥር ፫—፲፫ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ የተመኘችው ስብሰባ ተደረገ ፤ በዚህም ስብሰባ ላይ የተካፈሉት ፤

፩/ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
፪/ የአንጾኪያ ኦርቶዶክስ » »
፫/ የአርመን ኦርቶዶክስ » »
፬/ የምሥራቅ ሶርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን (ሕንድ)
፭/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናቸው ።

እነዚህም አብያተ ክርስቲያናት ከ፩ሺህ፭፻፲፭ ዓመታት በፊት እንጂ ከዚያ ወዲህ በአንድነት ተገናኝተው አያውውቁም ነበር ስለዚህ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም የተደረገው ለምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ታላቅ በር ከፍቶአል ።

## ለጉባኤው የቀረቡት አጀንዳዎች

፩/ ቤተ ክርስቲያንና ዘመናዊው ዓለም ፤
፪/ በመንፈሳዊ ትምህርት አሰጣጥ ስለመተባበር ፤
፫/ በስብከተ ወንጌል ሥራ ስለመተባበር ፤
፬/ የአብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ፤
፭/ ለጉባኤው ጽ/ቤት ስለማቋቋም ፤
፮/ የዓለም ሰላም የሚሉ ነበሩ

ጉባኤውም ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አጀንዳ



www.ethiopianorthodox.org

ዎች ላይ ተወያይቶ በብዙዎቹ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ የቀሩትን ደግሞ ለሌላ ጊዜ በመቅጠር ስብሰባውን ፈጽሟል ። ይህ ዓይነቱ ግንኙነት በየጊዜው እንዲቀጥል ለማድረግ ጉባኤው ለጊዜው አንድ ጊዜያዊ ጽ/ቤት እንዲቋቋም ቢወሰንም እስከ አሁን የተደረገም ሆነ የታሰበ ሁለተኛ ስብሰባ የለም ። ቢሆንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይህ ግንኙነት ወደፊትም በይበልጥ እንዲቀጥል ከፍተኛ ምኞቷ ነው ።

## ከዓለም አብያተ ክርስቲያ ናት ጋር ያላት ግንኙነት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከ፲፱፻፴ ዓ/ ም ጀምራ በአፍሪካ አህጉር ራሷን ችላ ትምህርተ ክርስትና በራሷ ሰዎች ለራሷ ሰዎች ስታስተምር የቆየች ቤተ ክርስቲያን ናት ።

ከኬልቄዶን ጉባኤ ከ፬፻፶፩ ዓ/ም ወዲህ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ለግል ክብር ሲሉ የየራሳቸውን አሳብ በነገረ መለኮት ትርጉም በማሳበብ በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር ይህች ቤተ ክርስቲያን ልዩነት እንዲጠፉ ወደ አምላክ ስትጸልይ የቆየች ናት ።

የአብያተ ክርስቲያናት አንድነት ማኅበር ለማቋቋሚያ ምክንያት የሚሆን ጉባኤ በ፲፱፻፳፪ ዓ/ም በኤደንብራህ ላንድ ስኮት የዓለም የወንጌል መልእክተኞች "እምነትና ሥነ ሥርዓት" በሚል ርእስ የመጀመሪያውን ስብሰባ አደረገ ይህ ዓይነቱ ስብሰባ በተለያዩ ሀገሮች እስከ ፲፱፻፴፱ ዓ/ም ድረስ ፫ ጊዜ ስብሰባ ከተደረገ በኋላ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም በአምስተርዳም ሆላንድ የመጀመሪያ የቤተ ክርስቲያናት ታላቅ ጉባኤ ከ፩፻፵፯ አባላት ቤተ ክርስቲያን የተወከሉ ፫፻፲፭ የቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች ተገኝተው ማኅበሩን ሲያቋቁሙ ከመሥራች አባላት አንዷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት ።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ከተቋቋመ ወዲህ በተደረጉት አያሌ ከፍተኛ ስብሰባዎች ሁሉ መልእክተኞቿን እየላከች ግንኙነቷን በማጠንከር በክርስቶስ የተመሠረተችው አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሆና ሳለ በመሪዎች አርቆ አለማሰብ የተነሳ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል በቃላት ትርጉም ምክንያት የተፈጠረው አለመግባባት ተራርቀው የቆዩትን ሁሉ እየተቀራረቡ ልዩነታቸውን በመጠኑ እንዲተው ማኅበሩ ረድቶአል ለአንድ ዓይነት ሥራም በኅብረት እንዲሰለፉ አንቅቶአቸዋል ። ለዚህም ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የሥራ ድርሻ አበርክታለች የተላለፉትንም ውሳኔዎች ሁሉ በሥራ ላይ አውላለች በዚህም ምክንያት ግንኙነቷ ከቀን ወደቀን እየቀጠለ ሄዷል ።

## የዓለም አብያተ ክርስቲያ ናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ

አባላት አብያተ ክርስቲያናት በሚገኙበት አገሮች ባምስቱ ወይም በየ፯ቱ ዓመታት በየተራ ስብሰባ ስለሚያደርጉ ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ከመሥራች ዓባላት አንዷ በመሆኗ ፪፻፴፰ አብያተ ክርስቲያናት በአባልነት የሚገኙበት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ ከጥር ፩ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም በአዲስ አበባ ስብሰባ ሲያደርግ አስተናጋጅዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነበረች ። በዚህም አጋጣሚ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያን የክርስቲያን ደሴት ተብላ የተጠራችበትን ያስጠራቻት ቤተ ክርስቲያን የራሷ ዜማ ሥዕል ፤ ሥነ ጽሑፍ ያላት የራሷንም ምእመናን በራሷ ቋንቋ የምታስተምር ጥንታዊ ቅርጻ ቅርጽ የተቀደሰ ባህልና ልማድ ያላት መሆኗን አሳይታለች ።

በቀረበውም አጀንዳ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ከልማት ተግባር ጋር ለመራመድ እንዴት እንደምትችል ፤

፩/ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደቀ መዛሙርት የነጻ ትምህርት ዕድል እንዲሰጥ በተወሰነው መሠረት በአሁኑ ሰዓት በወዳጅ አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ ትምህርት የሚከታተሉ ፻፲፰ ተማሪዎች አሏት ።

፪/ መንፈሳዊ ድርጅቶች ተቋቁመው በልማት በኩል ስለሚኖራቸው ተሳትፎ ተነጋግረው ውሳኔ በመስጠትና ጉባኤው በይበልጥ ሰፊ ውይይት በማድረግ ከልዩ ልዩ የሃይማኖት ድርጅት ጋር የተቀራረቡ ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ውይይት እንዲጀመር ተወስኗል ። በዚምህ ስብሰባ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአባልነት ለመመዝገብ መልካም ምኞቷን ገልጻለች እንዲሁም በአዲስ አበባው ስብሰባ ላይ ፲፫ አብያተ ክርስቲያናት በቋሚ ማኅበርተኛነት ተመዝግበዋል ። የአባላቱም አብያተ ክርስቲያናት ቊጥር ፪፻፴፰ አብያተ ክርስቲያናት ሆነዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

፬/ የ፫ኛው ዓለም ሕዝቦች ነጻነታቸውን የሚቀዳጁበትን ዕድል እንዲያገኙ በትምህርት በዐሣብ መርዳትና የሰለጠኑት መንግሥታትም ለጨቋኝ ዘረኛ መንግሥታት የጦር መሣሪያ እንዳ ይሸጡ የሚል ውሳኔ አሳልፈዋል ።

(ከዚህም በላይ የተጠቀሰው በትንሣኤ መጽሔት በቊጥር ፯ ላይ ይገኛል ።)

## የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የመገናኛ ዘዴዎች ማኅበር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ባላት ግንኙነት መሠረት ርዳታ የሚደረግላት መሆኑ የታወቀ ነው ።

በዚህ ምክንያት ቀደም ብሎ ለትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ሕንጻ ማሰሪያና አዳዲስ የማተሚያ መኪናዎችን መግዥያ የሚሆን ርዳታ ጠይቃ ነበር ። በዚህ ምክንያት የድርጅቱ ክፍል አሁን (ዋክ) የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የመገናኛ ዘዴዎች ማኅበር የኅትመት የመገናኛ ክፍል እርዳታውን ስለሚሰጥበት ሁኔታ እንዲያጠና አንድ ኤክስፐርት በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ልኮ ስለማ/ቤቱ ሁኔታ ካጠና በኋላ ማ/ቤቱን ለመርዳት እንዲቻል አስቀድሞ አንድ ዘመናዊ የማሳተሚያ ድርጅት እንዲቋቋም እቅድ አዘጋጀ ።

በዕቅዱ መሠረት ዋክ እስካሁን ሦስት ሠራተኞችን በማሳተሚያው ድርጅት አሰልጥኗል ለወደፊትም ለማተሚያ ቤቱና ለማሳተሚያው ድርጅት ሠራተኞችን ያሰለጥናል በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ለማ/ቤቱ ሁለት ሠራተኞች ለማሳተሚያው ድርጅት አንድ ሠራተኛ ያሰለጥናል ከዚህ በስተቀር ለማሳተሚያው ድርጅት አስፈላጊውን የማቋቋሚያ ገንዘብ ይረዳል የሠራተኞችንም ደመወዝ በመክፈል ላይ ይገኛል ።

ከዚህ በቀር ለማተሚያ ቤቱና ለማሳተሚያው ድርጅት የሚያገለግል ሕንጻ ለማሠራት ተዘጋጅቶአል እንዲሁም በየደረጃው ለማ/ቤቱ ፤ አስፈላጊ የሆኑትን መኪናዎች መግዣ የሚሆን ገንዘብ ለመስጠት በጐ ፈቃድ እያሳየነው ።

የማሳተሚያው ድርጅት ሁለት ዓይነት መጻሕፍት ያሳትማል እነዚህም ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ የሆኑትንና ጠቅላላ ብዙኃኑ ሕዝብ ሊጠቀምባቸው የሚችሉትን መጻሕፍት ያዘጋጃል (ዋክ) ድርጅቱን የሚረዳው ቤተ ክርስቲያን ለሕዝብ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንድትችል ለመርዳት አስቦ ነው ። (ዋክ) W.A.CC. በጠቅላላ ለድርጅቱ እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ለመርዳት አስቦአል ።

## ልማት ኮሚሽን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዓባል በመሆኗ በቤተ ክርስቲያኗ አቋምውስጥ አንድ የልማትኮሚሽን እ/አ/ዘ/አ/ በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ተቋቁሞአል፤ይህም ኮሚሽን በቤተ ክርስቲያኒቷ ውስጥ ለሚያገለግሉት ካህናት ከዘመናዊ ሥልጣኔ አረማመድ ጋር የሚራመዱበትን በኤኮኖሚ ፥ በትምህርት የማኅበራዊ ኑሮ በልማት ተደራጅተው ለኅብረተሰቡ ልማትን ከሃይማኖት ትምህርት ጋር አጣምረው እንዲያስተምሩ የሚረዳ ነው፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፲፰ሺህ አብያተ ክርስቲያናትና ፪፻ሺህ ካህናት አሏት እነዚህንም ካህናት በልዩ ልዩ ትምህርት የሚያደራጃቸው ይህ ኮሚሽን ነው ፤ ኮሚሽኑ ስደተኞቹንም በሚገባ ይከባከባቸዋል ፥ ይህ ዓይነቱ ሥራም ከቤተ ክርስቲያን ሥራ አንዱ ነው ።

## የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ማኅበር

በአፍሪካ አህጉር በሚገኙት ሀገሮች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አህጉራዊ ማኅበር አላቸው ። ይህም የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ማኅበር ነው ። ከነዚህም ማኅበር መሥራች አብያተ ክርስቲያናት አንዷ የኢትዮጵያቤተክርስቲያን ናት ይህም ማኅበር በአፍሪካ አህጉር የሃይማኖትና የልማት ትምህርት ጎን ለጎን እንዲራመድ የሚረዳና የሚያስተምር ማኅበር ነው ። ይህም ማኅበር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በመገናኛ ዘዴዎች ለሚያገለግሉ ሠራተኞች እስኮላርሺፕ እየሰጠ በሬዲዮ በቴሌቪዥን በሥነ ጽሑፍ በየዓመቱ ያሠለጥንላታል ፤ በዚህም የመገናኛ ዘዴዎችን ከመቸውም በበለጠ መጠቀምን ጀምራለች ፤ ከዚህም ሌላ ይኸው ማኅበር በልማት የሚሠሩትን ሠራተኞች እንደ ከተማ ሐዋርያ ያሉትን አገልጋዮች ያሠለጥንላታል ።



www.ethiopianorthodox.org

ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፤ ጋር ባላት ግንኙነትም ፤

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የነጻ ትምህርት እየሰጠች ተምረው ሲመለሱ ቤተ ክርስቲያናቸውን በይበልጥ ያገለግላሉ ።

## የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን

ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት እንደ መባሏ መጠን የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን የዓለም አብያተ ክርስቲያን ማኅበር አባል ድርጅት በመሆኑ በአ- አ- ብሥራተ ወንጌል የሚባል አንድ ራዲዮ ጣቢያ አቋቁሞ የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ/ ም አስመርቋል ። ይህ ራዲዮ ጣቢያ የእግዚአብሔር ቃል ላልደረሳቸው ለማዳረስና ክርስቲያናዊ ትምህርትንና ልማትን በሬዲዮ ለማዳረስ ነው ። ይህም የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ስምምነት ሲፈራረም ፤ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የ፲፫ ደቂቃ በቀን የሬዲዮ ፕሮግራም እንድታስተላልፍ ሰጥቶአል ።

በዚህም መነሻ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሬዲዮ ስብከትና የመገናኛ ዘዴዎች ማጠናቀሪያ የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ተቋቁሞ የሬዲዮ ስቱዲዮው ሥራውን በሚገባ ሲያካሂድ ቆይቶአል ፤ የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅትን በየጊዜው በአሳብ ፤ በገንዘብ ፤ በፕላን ፤ በጉልበት ፤ በትምህርት በየጊዜው ይረዳል ፤ በየጊዜው ከሚለግሰው ርዳታ የተነሣ የድርጅቱ ሥራ ከቀን ወደ ቀን እያደገ ሄዷል ፤ ከ፲፫ ደቂቃ ወደ ፩ ሰዓት ከ፴ በቀን ያስተላልፋል ። በቅርብ ጊዜ በአማርኛ በትግርኛና በኦሮምኛ በግዕዝ ቋንቋ በቀን ፪፡፳፭ ለማስተላለፍ በመዘጋጀት ላይ ነው ።

ስኮለርሽፕም በመስጠቱ የድርጅቱ ሠራተኞች እየተማሩ ሲመለሱ ድርጅቱን ያገለግላሉ ለዚህም ርዳታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታመሰግናለች ።

የጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያንም

የሐዋርያዊ ድርጅት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመገናኛ ዘዴዎች ማደራጃ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን በስብከተ ወንጌል ያላትን ተሳትፎ ለምእመናን በብሥራተ ወንጌል ራዲዮ ጣቢያ በሚገባ ለማሠራጨት የምትዘጋጅበትና የምታጠናቅርበት አንዱ መጠነኛ የማስሚዲያ ሴንተርን ሕንፃ በአንድ ሚሊዮን ብር ለማሠራት ስለታሰበ ግማሽ ሚሊዮን ብር የጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ለመርዳት አስባለች ። የሚሠራውም ሕንፃ ፦

ሀ/ ፫ የሬዲዮ ስቱዲዮ

ለ/ ፩ የኦዲዮቪዥዋል ስቱዲዮ

ሐ/ የሥነ ጽሑፍ ማደራጃ ክፍል

መ/ እንዲሁም የወጣቶች እንቅስቃሴ ክፍል

ይኖረዋል ።

ከዚህም ሌላ የጀርመን ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ትምህርት እንዳይጠፋ በማሰቧ የቤተ ክርስቲያን ት/ቤት እያቋቋመች ኢትዮጵያውያንን ትረዳለች ፤ ታስተምራለችም ፤ የነፃ ትምህርትም ትሰጣለች፤ ይህን የመሳሰለውን ርዳታ በጀርመን ቤተ ክርስቲያን በኩል የሚረዳ «ብሬድ ፎር ዘወርልድ» በተባለው ድርጅት አማካይነት ነው ።

በሀገር ውስጥ ካሉት ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላት ግንኙነት ከመቸውም በበለጠ እየቀጠለ ሄዷል ። የኢትዮጵያ መ/ቅዱስ ማኅበር አባል ከመሆኗም ሌላ ይህምበኢትዮጵያ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት አንድ ብሔራዊ ክርስቲያናዊ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ለማቋቋም ሲታሰብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አሳቡን ሙሉ በሙሉ ደግፋ ይኸንኑ ከሚያጠናው ጊዜአዊ አጥኚ ኮሚቴ አባሎች የሚሆኑ ወኪሎች ልካ በኢትዮጵያ ያሉት ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት በማኅበር ጉባኤ የሚያቋቁሙበትን ቀን ትጠባበቃለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ውጭ ፣ በርከት ያሉ ምዕመናን አሏት የቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት ተፈላጊና ጥንታዊ መሆኑን ልዩ ልዩ ሀገሮች ያምኑበታል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎች በልዩ ልዩ ሀገሮች ተሠርተዋል ለማስረጃ ያህል በሱዳን ፣ በለንደን ፣ ባሜሪካ፥ በካናዳ፥ በጃማይካና ትሪንዳድ አሏት የነዚህም ቤተ መቅደሶች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አማንያን አሏቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ በውጭ አገር መፈለግን የሚያስረዳ ነው ። የኬንያ መንግሥትም በናይሮቢ አንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ማሰሪያ ቦታ ሰጥቷል ።

በዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲን ግንኙነቷን ከዕለት ወደ ዕለት እየቀጠለች በመሄዷ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ አርአያ በመሆን ላይ ትገኛለች ።



www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላት ግንኙነት

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር ያላት ግንኙነት በጣም አስደሳችና ታሪካዊም ነው ። በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ባለው መልካም ግንኙነት የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት የነጻ ትምህርት ዕድል በመስጠት አያሌ ካህናትንና ሰባኪያንን በማሠልጠን ስትረዳ ቆይታለች ። በመሠረቱ የግሪክ ቋንቋ የቲዮሎጅ ቋንቋ ስለሆነ በዚህ መስክ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን ጋር የምታደርገው ግንኙነት በብዙ ነገር ረድቷታል ።

# በሶሻሊስት አገሮች ከሚገኙት አብያተክርስቲያናት ጋር ያላትግንኙነት

ከሩሲያ ጋር የቆየ ግንኙነት ፤ እንደ ኤ. ዘ. አ. በ፩ሺ፫፻፷፰ ዓ/ም የዛሬ ፺፻ ዓመታት ገደማ ላይ የሩስያ መንፈሳውያን መምህራን የኢትዮጵያን መንፈሳዊ ዜና በመስማታቸው ከሃገራቸው ተነሥተው ኢትዮጵያውያን መነኲሳት በብዛት ይገኙበት በነበረው ወደ ኢየሩሳሌም ገዳም መጥተዋል ፤ እነዚህም መንፈሳውያን ምሁራን ስለኢትዮጵያ መንፈሳዊ ታሪክ ባህልና ጥንታዊነት ጥሩ አድርገው ከአጠኑ በኋላ ፐዝኒ ያኮቭ የተባለው ተጓዥ በአዘጋጀው መጽሐፍ«የኢትዮጵያ ምእመናን በፍልስጥኤም» በሚል ርእስ ስለኢትዮጵያ ዋጋ ያላቸውንና አስደናቂ ታሪኮችን ጽፎ አቅርቧአል ።

የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ባህል እጅግ አድርጎ የማረከው የትኛው እንደሆነ ታሪኩ ላይ ሲገልጽ የኢትዮጵያውያን ያላቸው የጸሎት ሥነ ሥርዓት እጅግ የሚያስደስት ከመሆኑም በላይ የዜማውና የቋንቋው ፤ የወረብ ፤ መንፈሳዊ ሽብሸባና ውዝዋዜ እጅግ አድርጎ ሕሊናውን በመንፈሳዊ ስሜት እንደመሰጠው አስፋፍቶ ጽፎታል ። ከዚህ በላይ ጸሐፊው በሰጠው ኃይለ ቃል ላይ «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያላት መንፈሳውያን ዜማዎችና የእነዚሁ የአቀራረብ ሥርዓት በሰብአዊ አካል ውስጥ የሚተላለፍ ድምፅ ሳይሆን የመልአክትን ምስጋናና ድምፅ የመሳሰለ ነው ብሎአል ።

በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመንም በሞስኮ ውስጥ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ስነ ሥርዓት በሞስኮ ቋንቋ ተዘጋጅቶ በሕዝብ እጅ እንዲዳረስ ስለተደረገ ሶቭየቶች በዚያን ጊዜ ስለኢትዮጵያ ብዙ መረጃና ጥናት በመከታተል ስለኢትዮጵያ የበለጠ ለማወቅ ችለዋል ።

በ፲፮፻፹፩ ዓ/ም ዮቢስ የተባለው የጀርመን ተወላጅ በሞስኮ ሀገር ላይ «ሂስትሪ ኦፍ አቢሲንያ» የአቢሲኒያ ታሪክ በሚል ርእስ አትሞ ያወጣውን መጽሐፍ በዘመኑ የነበሩትን የነገሥታት ሥልጣን ከፍተኛ አድናቆትና ግምት ሰጥቶታል ።

የኢትዮጵያን ታሪክ አንብቦ በጣም የተደሰተው አንድ ሲዊዲን ምሁር ሰፑር ቤን ቤልድ ለሩስያው መሪ በደብዳቤ አመስግኖ ልኮለት እንደነበረ ታሪክ ይናገራል ። ይኸው ሰው ጽሑፉ በመስኮብኛ ቋንቋ እንዲታተም አሳስቦ ስለነበር የመስኮቡ መሪ ቀ/ /ጴጥሮስ በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ኒኮላስ ስፓፋራዶል በተባለው ግሪካዊ ተወላጅ አማካይነት የበላይ ጠባቂ ሆኖ ተተረጐመ ። ስለዚህም ኒኮላስ በመስኮብ ውስጥ እጅግ በጣም የታወቀ ከፍተኛም ዝና የነበረው ሰው ከመሆኑም ሌላ በቻይና ሀገርም የሩሲያመንግሥት አምባሳደር ሆኖ ሠርቷአል ።

ይህች ቤተክርስቲያን በኅብረት ሰባዊነት በሚመሩት አገሮችም ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ከፍተኛ ወዳጅነት አላት የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክሳዊት እንደመሆኗ መጠን ኢትዮጵያውያንን በማስተማር ልዩ ልዩ ርዳታም ለማድረግ በጉብኝትም ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት የጠለቀ ግንኙነት አላቸው ።

የሩማንያና የቡልጋርያ አብያተ ክርስቲያናትም

እንደዚሁ ኦርቶዶክሳውያን ስለሆኑ ለቤተ ክርስቲያናችን አገልጋዮች የነጻ ትምህርት በመስጠትና በልዩ ልዩ ታሪካዊና ባህላዊ ልውውጦችን በማድረግ ግንኙነት አላቸው ።

ከክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ጋር ያላት ግንኙነት

በሶሻሊስት ሀገሮች የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ከ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ወዲህ C.P.C. በመባል የታወቀ ድርጅት አላቸው ። ድርጅቱም በዓለም ሰላም ስለሚሰፍንበት ሁኔታ ለመወያየት በየአምስት ዓመቱ ስብሰባ ያደርጋል ። ከ፲፱፻፶፱ ዓ/ም ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድርጅቱ በሚያደርጋቸው ጉባኤዎች ላይ ተካፋይ ሆናለች በተለይ ከ፲፱፻፷፬ ዓ/ም ወዲህ የድርጅቱ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሆና ስትሠራ ቆይታለች ።



www.ethiopianorthodox.org

የ፫ኛው ፓትርያርክ በዓለ ሢመት ።

# የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ተሐድሶ ፤

ከፍቅረ ድንግል በየነ

በቀድሞው የኢትዮጵያ ሥርዓት ማኅበርና የአስተዳደር ዘይቤ የቤት ክርስቲያንናየመንግሥትግንኙነት እጅግ የተሳሰረ በመሆኑ ነገሥታቱና መኳንንቱ የመንግሥቱንና የቤት ክህነቱን የአስተዳደር ሥልጣን አጣምረው ይዘው ማቆየታቸው በታሪክ የተረጋገጠ ነው ።

የቤት ክርስቲያን መተዳደሪያ ሀብት የሚገኘው ነገሥታቱ በችሮታ ከሚለግሡት የመሬት ርስትና ጉልት ሲሆን የመሬት ሥሪት የተለያየ በመሆኑ አንዱ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጋሻ መሬትና ቀላድ ሲኖረው ሌላው ደግሞ ገጠር የመባል ስም ተሰጥቶት በድኅነት ሲሰቃይ ቆይቷል ። ከዚህም በላይ መሳፍንቱና መኳንንቱ እልቅናውንና ግብዝናውን ርስት አድርገው ስለሚይዙት ፡ በብዙ ሺ. የሚቆጠሩ ቀላዶችና ጋሻ መሬቶች በተዘዋዋሪ መንገድ ተመልሰው ወደ ልዑላኑ እጅ ይገባሉ ፡ ወይዛዝሮቹ ባህሉና ሥርዓቱ የማይፈቅድላቸውን የቤት ክርስቲያንን የሹመት መዐርግ በተጽእኖ እየያዙ ምሁራን ካህናትን በትንሽ አበል እየገዙና «ቶፋ» የሚል የዝቅተኝነት መጠሪያ ስም እየሰጡ ሲያስገብሩት ኖረዋል ። በዚህ ምክንያት ስሙ የቤት ክርስቲያን ጥቅሙ የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ሆኖ ቆይቷል ።

ካህኑም በነበረበት የአስተዳደር ተጽእኖ እየተገፋ የዕለት ገቢ ለማግኘት በየክብረ በዓላቱ ግሥ እየገሠሠ፤ወረብ እየወረበ በማመስገን በኅብረተ-ሰቡ ማህል የመሳፍንቱና የነገሥታቱ ግርማ ሞገስ እንዲኖረው አድርጓል ።

በፍርድና በአስተዳደርም ጊዜ ፍትሐ ነገሥት በመተርጐም ፡ የጽሕፈት ሥራ በመሥራትና አንዳንድ አስተያየቶችን በመስጠት ካህናት የቤት መንግሥት ተችዎች ሆነው ከመቆየታቸውም በላይ ቤት ክርስቲያን የዜማ፡የቅኔ የመጻሕፍትና የፍልስፍና ትምህርት መገኛ እንድትሆን በማድረግ ካህናት ኅብረተሰቡን ሲያስተምሩ ቆይተዋል ።

## ቤተ ክርስቲያን በወደቀው መንግሥት ዘመን ፤

በወደቀው ከፊል ፊውዳል ሥርዓት ቤት ክርስቲያን በቆየው ሥርዓት መሠረት በጳጳስና በእጨጌ ትተዳደር ነበር ። ጳጳሱ ሥልጣነ ክህነትን ሲሰጡ እጨጌው ደግሞ የአስተዳደሩን ሥራ ይመሩ ነበር ።

ነገር ግን የፓትሪያርክነት ሥልጣን ከተጀመረ የእጨጌነቱን ሥልጣን ለፓትሪያርኩ ተደርቦ በመሰጠቱ አስተዳደሩ ከቀን ወደ ቀን እጅግ እየከፋና እየተበላሸ መሄድ ጀመረ ።

የሊቃነ ጳጳሳቱና የጳጳሳቱ ደመወዝ እጅግ እየናረና እየመጠቀ ሲሄድ የሊቃውንቱ፡የመምህራኑና የካህናቱ አበል ግን በሚያሳዝን ሁኔታ እያዘቀዘቀ፡ እየቆለቆለ በመሄድ ከፍተኛ የመደብ ልዩነትን ማስከተሉ ብዙ ሊቃውንትና ምሁራን በችግር ምክንያት ከቤት ክርስቲያን እንዲሰደዱ አድርጓል ።

ጥቂት ተጠቃሚዎችና አድር ባዮች ከቀድሞው ጽሕፈት ሚኒስቴር በሚታዘዝላቸው ተደራራቢ የገንዘብና የመኪና ስጦታ ፡ ኀላፊነታቸውን እስከ መርሳት ደርሰው የጭቁኑን ካህን ኑሮ በመጨቆን ራሳቸውን የገዥው መደብ መሣሪያ አድርገው መኖርን መረጡ ።

ስለዚህ ድኃ ሲበደል ፍርድ ሲጓደል ፡ መንፈሳዊ ግዴታቸው ለፍርድና ለርትዕ እንዲቆረቆሩ ሊያስገድዳቸው አልቻለም ። በአገራችን ረሀብ ገብቶ ብዙ ሺ. ሰው ሲያልቅ በረሀብ ለሚሞተው ምግብና ውኃ ከማቀበል ይልቅ ከበዝባዡ መደብ ጋር መደሰትን መረጡ ። የቤት ክርስቲያንን መሬት መሳፍንቱና መኳንንቱ ሲካፋፈሉት የእነሱ ግብር አበር በመሆን የተቻላቸውን ያህል ዘርፈው ያዙ እንጂ



www.ethiopianorthodox.org

አድራጎቱን አላወገዙም። በዚህም ምክንያት የጭቁኑ ካህን ድምፅ ወደ እግዚአብሔር ስለ ጮኸ ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት አማካይነት የጠም አደሩ ካህን ንቃትና ተሐድሶ ሊያገኝ በቅቷል ።

## ዐዲሱ መንፈሳዊ አስተዳደር

ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና በኢትዮጵያ የተደረገው ሕዝባዊ እንቅስቃሴና አብዮት ባስገኘው ኃይልና ድል ፥ ከበዝባዦቹና ከአድር ባዮች ዋና ዋናዎቹ ደክመዋል ። ከእንግዲህ ወዲህ አስተዳደሩን በተሐድሶ ማቃናት በሐቅ ለሚኖሩት ካህናትና ምዕመናን ተቀዳሚ ተግባር መሆን ይገባዋል። እስከ ዛሬ ድረስ ኑሮውን በልመናና በቅልውጥ እንጀራ ላይ መሥርቶ የቆየው ጭቁኑ ካህን መብቱንና ግዴታውን የሚያስከብርበትና የሚጠብቅበት ጊዜ እንሆ አሁን ነው ።

ዛሬ አስተዳዳሪዎቻችንን የሚሾሙልን ለግል ጥቅማቸው የሚያስቡት ነገሥታትና መሳፍንት አይደሉም ፤ እኛው ከመካከላችን ሊያገለግለን የሚችለውን ጠንካራውንና ታማኙን እንመርጣለን ። ይህም በአሁኑ የፓትሪያርክ ምርጫ የተመሠከረለትና የተረጋገጠ ሐቅ ነው ። ተገዝተው የሚገዙንና የሚያስገዙን ሹማምንት ከእንግዲህ ምንም ቢሆን በአስተዳደራችንና በገንዘባችን አይቀልዱበትም ። የጨበጥነው ዲሞክራሲያዊ መንፈሳዊ መብት ከእጃችን በምንም ምክንያት ሊወጣ አይችልም ። ስለዚህ የአስተዳደሩ ተሐድሶ ወደፊት ይቀጥላል ።

## መንፈሳዊ ምክር ቤት

በግለሰቦችም ሆነ በክፍላተ ሀገር ወይም በማናቸውም ረገድ አድልዎንና ልዩነትን ለማጥፋት ፥ መብትና ግዴታን እኩል ለመካፈል የሚቻለው በብዙኀን የተመረጡ አዋቂዎች አማካሪዎች ያሉበት አንድ ከፍተኛ መንፈሳዊ ምክር ቤት ሲቋቋም መሆኑ የታወቀ ነው ይህም ምክር ቤት የአስተዳደሩ ርእስ እንደ መሆኑ መጠን የየክፍላተ ሀገሩ ካህናትና ምእመናን ከመካከላቸው በሚመርጣቸው የምክር ቤቱ አባሎች አማካይነት የአስተዳደሩ ተካፋዮች ሆነው የሚሳተፉበት ነው ።

የአባሎቹ ምርጫ ያለ ምንም ተጽእኖ ፍጹም ሐቀኛና ትክክለኛ በሆነ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መከናወን ይገባዋል የምክር ቤቱ መቋቋም ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች እጅግ ጉላ ብሎ የሚታየው የአዲሱ «ሕገ ቤተ ክርስቲያን» መውጣት ሊሆን ይችላል ።

እንደሚታወቀው ማናቸውም ጉድለት የሚቃናው በሕግ መሆኑ ግልጽ ነው ። እስከ ዛሬም ለቤተ ክርስቲያናችን አስተዳደር አብነትና መርህ የሚሆን የመተዳደሪያ ደንብ ሳይኖር በዘልማድ ሲሠራ መቆየቱ አግባብ አልነበረም ። አሁንም ይሕ ችግር ሊፈታ የሚችለው በምክር ቤቱ መቋቋም መሆኑ አያጠራጥርም ።

## ሰበካ ጉባኤ

የሰበካ ጉባኤ መቋቋም አሳብ ቀደም ብሎ የተጀመረ መሆኑ ይታወሳል ። ይሁን እንጂ እስከ ዛሬ ድረስ በየቤተ ክርስቲያኑ ከሚሾሙት አለቆች አብዛኛዎቹ የበዝባዦቹና የዘራፊዎቹ ሹማምንት አቀባባዮችና የስርቆት መሣሪያዎች ስለ ነበሩ በየሰበካቸው ሊቋቋም የሚገባውን የሰበካ ጉባዔ ሲያዳክሙና ሲበትኑ ቆይተዋል

ስለዚህ የተዳከመው የሰበካ ጉባኤ አቅዋም በአስቸኳይ ካልተጠናከረ በብዙ አቅጣጫ ቤተ ክርስቲያንን ሊጎዳት ይችላል ። የእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደር መሻሻልና በኤኮኖሚ መጠንከር የጠቅላላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መሆኑ መታወቅ አለበት ፤ ስለዚህ ምእመናንና ካህናት በየአጥቢያቸው የሰበካ ጉባዔያቸውን ማቋቋም አለባቸው ። የዋናው ምክር ቤት አቅዋም ሊጠናከርና ኃይል ሊያገኝ የሚችለውም በሰበካ ጉባኤያቱ ብርታትና ድጋፍ መሆኑ አያጠራጥርም ። ሰበካ ጉባዔዎችን በአስቸኳይ ለማቋቋም የተጀመረው ዘመቻ መፋጠን አለበት ።

### የገቢ ምንጭና የመተዳደሪያ ሀብት

#### ሀ- ትሩፋት

ስለ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ሀብትና የገቢ ምንጭ በምናሳስብበት ጊዜ በቅድሚያ የሚታወሰን የምእመናኑ ትሩፋት ነው ። ይህም ትሩፋት የምንለው ምዕመናኑ በግል ፈቃዳቸው ቀስቃሽነት ተነሳስተው በፍቅረ እግዚአብሔር ተጸምደው የሚሰጡት ችሮታ ነው ። ይህም ትሩፋት በሙዳየ ምጽዋት ፥ በስዕለት ፥ በማኅበረተኝነት፥በመዋጮና በመሳሰሉት መንገዶች የሚደረግ ልግስና ነው ። ይሁን እንጂ የስጦታው መጠን እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ማድረግ የሰባክያኑና የመምህራኑ የሥራ ድርሻ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ የተሰበሰበው ገንዘብ በጥንቃቄና በሥርዓት እንዲያዝ ማድረግና ሂሳቡን መቆጣጠር የምእመናኑም ግዴታ ነው ። ይህን ሲመለከቱት የቤተ ክርስቲያንን ገቢ ማዳበር በተቀዳሚ የሰበካ ጉባኤው ተግባር ሆኖ እናገኘዋለን ። ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ደግሞ በሀብታሞች አብያተ



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያናትና በድኆቹ መካከል ያለው ልዩነት ነው ። በጉልህ እንደሚታየው በከተሞች በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና በገጠር በሚገኙት መካከል የሀብት ልዩነት አለ ። በገጠርየሚገኙት ድኆች ናቸው ።

ስለዚህ ልዩነቱን ማስወገድ ወይም ማቀራረብ አስፈላጊ ግዴታ ነው ። ለዚህ ጉዳይ መፍትሔ እን ዲሆን የታሰበው አንድ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ማቋ ቋም ነው ። በዚህም ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ተቀማጭ የሚደረገው ገንዘብ ከሀብታም ሰበካዎች የሚገኘው ትርፍ ገንዘብ ነው ፤ ይህም ትርፍ ገንዘብ በማዕከ ላዊው ግምጃ ቤት ተቀማጭ የሚደረገው ገንዘብ ከሀብታም ሰበካዎች የሚገኘው ትርፍ ገንዘብ ነው ገንዘቡም በማእከላዊው ግምጃ ቤት እየተጠራቀመ ገቢ ለሌላቸው ሰበካዎች ይደለደላል ።

## ለ- የሥራ ውጤቶችና የልማት ዘርፎች

ቀሳውስትና መነኰሳት ከጸሎትና ከቅዳሴ የተ ረፈውን ጊዜያቸውን በሥራ ላይ እንደሚያውሉት የታወቀ ነው ። ነገር ግን ይህን የካህናቱን የጉልበት ኃይል በሥራ ላይ ለማዋል በቂ የሥራ መስክ መክ ፈት ያስፈልጋል ።

ስለዚህ የሚከተሉት የሥራ ዘርፎች ለካህናቱ የሥራ እድል ከማስገኘታቸውም በላይ የገቢ ምንጭ ለመሆንም ይችላሉ ።

**፩፡ ማተሚያ ቤቶች ፤** የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቁጥራቸው እጅግ የበዛ መጻሕፍት ያሏት ከመሆንዋም በላይ ብዙ መጻሕ ፍት ገና በማኅተም ያልተጻፉ መሆናቸው ይታወ ቃል ።

የተጀመረው የኅትመት ሥራ ቢስፋፋ ጥቅሙ እጥፍ ድርብ መሆኑ ይሰማናል ፤ በአንድ በኩል የሥራ መስክ ለካህናት የሚከፈት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከመጻሕፍቱ የሚገኘው ጥቅምና ከሽያጫቸው የሚ ገኘው ገቢ ለሥራው የሚደረገውን ወጪ ለመሸ ፈን ይረዳል ።

**፪፡ የተግባረ እድ ውጤቶች ፤** በአንዳንድ አብ ያተ ክርስቲያናት ቅጽረ ግቢ ውስጥ የተጀመሩት የምንጣፍና የሙካሽ ሥራዎች እንዲስፋፉና እንዲ ጠናከሩ እየተደረጉ ካህናትን በሥራ ላይ እንዲሠማሩ ለማድረግ ይረዳሉ ። በአክሱም ያለውን የእደ ጥበብ ሥራ ድርጅት ፤ የመቀሌው የሽማ ሥራ ድር ጅት ፤ የአድዋው የፈትል ሥራ ድርጅትና እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ ከፍተኛ የሥራ መስኮች ከመሆና ቸውም በላይ ጠቃሚ የገቢ ምንጮች ሊሆኑ ይች ላሉ ፤ አሁን ከተጀመሩት የተግባር ድርጅቶች በሚ ገኘው ገቢ ላይ ሌሎች ተጨማሪ ድርጅቶች በተ ለያዩ ሥፍራዎች ማቋቋም ይጠቅማል ። ያለፈው ሰንካላ አስተዳደር ግን በእነዚህ ድርጅቶች እያመ ካኘ ከውጭ አገሮች ብዙ የእርዳታ ገንዘብ ከመሰብ ሰብ በቀር ድርጅቶቹ ራሳቸውን ችለው በሚገኘው ትርፍ ሌሎች ተመሳሳይ የተግባር ዘርፎች እንዲቋ ቋሙ አላሰበበትም ፤ ትርፉና የምርቱ ውጤት ወዴት እንደደረሰ የሚያስረዳ ተጨባጭ ማስረጃም ሊያቀ ርብ አልቻለም ። ካህናት እስከ ዛሬ የሚሠርዋቸው እንደቁም ጽሕፈት እንደ ሥዕልና እንደ ድጉሠት የመሳሰሉት ሁሉ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎች በመሆ ናቸው ሠራተኞቹ በርዳታ እየተደገፉ እንዲቋቋሙ ያስፈልጋል ።

**፫፡ አገር ጐብኝዎች ፤** እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ አገር ጎብኝዎችንና ቱሪስቶችን የሚስቡት የቤተ ክርስቲያናችን ጥንታውያን ንሕፃዎችና ንዋ ያተ ቅድሳት መሆናቸውን ከቀድሞ ጀምሮ ኢትዮ ጵያን እየጐበኙ የተመለሱ ሁሉ የመሰከሩት ሐቅ ነው ። ነገር ግን በገቢው የሚጠቀመው ሌላ ድር ጅት መሆኑ ይታወቃል ። ስለዚህ ማንኛቸውም ድር ጅት በቤተ ክርስቲያናችን ንብረትና ሀብት የሚ ጠቀም ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ከሚያገኘው ጥቅም እንዲያካፍል ሕግ ያስገድደዋል ። ስለዚህ በዚህ መብት በመጠቀም የሚገኘው ገቢ በቀላል የሚገ መት ላይሆን ይችላል ። ከዚህም በላይ በተጨማሪ በታወቁት የታሪክ ቦታዎች በጠበል ቦታዎችና ቱሪ ስቶች በሚበዙባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ገንዘብን የሚ ያስገኙና የሚሸጡ ዕቃዎች እንዲዘጋጁ ቢደረግ ጥቅሙ እጅግ ብዙ ሊሆን ይችላል ።

## ፫፡ የወንዶችና የሴቶች ወጣቶች ድርሻ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ ያን በአስተዳደር፤ በስብከተ ወንጌልና በምጣኔ ሀብት ተሻሽላ ማየት የወጣቶቻችን የምንጊዜም ምኞት መሆኑ የታወቀ ነው ። ይህንንም ለመረዳት «የወ ጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት አጠቃላይ ጉባኤ» ከካህናትና ምእመናን አጠቃላይ ጉባዔ ጋር በመተ ባበር ስለ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያደረገውን ትግል መጥቀስ ይጠቅማል ።

ለወደፊቱም ቢሆን የተቋቋሙትን ማኅበራት በማጠናከርና ሌሎችም ተጨማሪ ማኅበራትን በማ ቋቋም መንፈሳውያን እንቅስቃሴዎችን በአዲስ መን ፈስ ለመጀመር ወጣቶቻችን ዝግጁዎች መሆና ቸው የታመነ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

መንፈሳውያን መዝሙሮች በዘመናዊ አቅድና
አቀራረብ አብዛኛውን ጊዜ ሊፈልቁና ሊገኙ የሚ
ችሉት በወጣቶች ማኅበራት አማካይነት ነው ።
ወጣቶች መንፈሳውያን ትምህርቶችንና የሃይማኖት
ሥርዓቶችን በእረፍት ጊዜያቸው ማጥናት ይገባቸ
ዋል ። ፕሮግራሞችና እቅዶች በማውጣት ስለ
ባህላቸውና ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናቸው መወ
ያየት አለባቸው ።

ከኢትዮጵያም ውጭ በጉብኝትና በትምህርት
መልክ እየተዘዋወሩ ለውጭ አገር ወጣቶች
ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ማስረዳት አለባ
ቸው እነሱም ስለ ሌላው ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ
የመረዳትን እድል ሊያገኙበት ይችላሉ ። በኢት
ዮጵያም ውስጥ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በማዘጋ
ጀት በእንግድነት የውጭ አገር ወጣቶችን መጋ
በዝ ሌላው ግዴታቸው ነው ።

ወጣቶች ለቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ርዳታ ለመ
ሰብሰብ ጠቃሚዎች ናቸው ። ልዩ ልዩ ድራማዎ
ችን በማዘጋጀትና የበዓላት ቀኖችን ምክንያት በማ
ድረግ በልዩ ልዩ ዘዴ ወጣቶች ለቤተ ክርስቲያን
ገቢ የሚሆን ገንዘብ ማስገኘት ይችላሉ እነዚህን
በመሳሰሉት ተግባሮች ወጣቶች ቤተ ክርስቲያንን
ለማገልገል የተዘጋጁ መሆናቸውም የታወቀ ነው።

# ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

## የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት አጠቃላይ ጉባኤ ፤

ከተሰማ አየለ

የነበረ ያለ ወደ ፊትም ዓለምን አሳልፎ የሚ
ኖር እግዚአብሔር አብ የተመሰገነ ይሁን ።

ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለርሱ ምንም ምን የሆነ
የሌለ እርሱ እውነት ፥ ፍቅር ፥ ዘለዓለማዊ ፥ የመ
ጀመሪያውና የመጨረሻው እግዚአብሔር ነው ።
በነቢያት አድሮ ትንቢትን ያናገረ ፥ በሐዋርያት
አድሮ ወንጌልንያስተማረ በቅዱሳንሊቃውንት አድሮ
መጻሕፍትን ያጻፈና ያስተረጐመ ልዑል ባሕርይ
እግዚአብሔር ፍርድ ሲጓደል፥ እውነት ስትረገጥ ፥
ፍቅር ስትኮሰስ ፥ ቅንነት ሲጠፋ ፥ ዓለም በኃጢ
አት ስታድፍ ፥ ደሀ ሲበደልና ሲጨቆን ዝም የማ
ይልና እውነተኛ ፈራጅ ነው ።

ለተሾሙ መንፈሳውያን አባቶች ግልገሎ
ቼን ፥ ጠቦቶቼን ፥ በጐቼን ጠብቁ ተብሎ
የተሰጠው ትዕዛዝ ሲዘነጋ ፥ ለሕዝብ አስተዳዳሪ
ዎችም «አሁንም እናንተ ባለጠጎች ስለሚደርስ
ባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ ! እያለችሁ አልቅሱ ሀብታ
ችሁ ተበላሽቷል ልብሳችሁም በብል ተበልቷል
ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጌል ዝገቱም ምስክር
ይሆንባችኋል ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል
ለኋለኛው ቀን መዝገብን አከማችታችኋል ፥ እነሆ !
እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደሞዝ በእና
ንተ ተቀምጦ ይጮሃል የአጫጆችም ድምፅ ወደ
ጌታ ፀባዖት ጆሮ ገብቷል በምድር ላይ ተቀማጥላ
ችኋል በሴሰኛነትም ኖራችኋል ለፍርድ ቀን እንደሚ
ያወፍር ልባችሁን አወፍራችኋል ፥ ጻድቁን ኰን
ናችሁታል ገድላችሁትማል» ተብሎ በሐዋርያው
ያዕቆብ የተነገረውና የተሰጠው ማስጠንቀቂያ አሳ
ተዋይ ሲያጣ አስቀድሞም ነቢዩ አሞጽ «በአ
ደባባይ የሚገስፀውን ጠሉ ፥ እውነትም የሚና
ገረውን ተፀየፉ ፥ ደሀውንም ደብድባችሁታልና የስ
ንዴውንም ቀረጥ ከርሱ ወስዳችኋልና ከተጠረበ
ድንጋይ ቤቶችን ሠርታችኋልና ነገር ግን አትቀ
መጡባቸውም ። »

«ያማሩ የወይን ቦታዎችን ተክላችኋል ነገር
ግን ከወይን ጠጃቸው አትጠጡም ። ጻድቁን የም
ትጨቁኑ ፥ ጉቦን የምትቀበሉ በበሩም አደባባይ
የችግረኛውን ፍርድ የምታጣምሙ እናንተ ሆይ
በደላችሁ እንዴት እንደበዛ ኃጢአታችሁም እን
ዴት እንደፀና አውቃለሁ» ተብሎ የተሰጠው ትን
ቢታዊ ፍርድ ሲናቅ እግዚአብሔር በየጊዜው ፥ በየ
ሃገሩ እውነተኛ ፍርዱን ሰጥቷል ።

በአገራችንም እነሆ የተበደለው የተገፋው ፍ
ርድ የጐደለበት ሕዝብ በመካስ ላይ መሆኑን እና
ያለን ቤተ ክርስቲያናችንም አስቀድማ በሕዝብ
ላይ የተመሠረተች ስትሆን በወደቀው የከፊል ጉል
ታዊና ባላባታዊ እንደዚሁም ከፊል ከበርቴ ሥር
ዓት ገዥዎች የፖለቲካና የሥልጣን መጠበቂያ
በመደረጓ እውነተኛ መልእክቷን የነጠረ እምነ
ቷን ለማስተላለፍና ለሰው ልጅ እኩልነት ለመጋ
ደል ሳትችል መቆየቷ ይታወሳል ።

ሕያው እግዚአብሔር የሕዝቡን መበደል የአ
ምልኮቱን መዘንጋት በመመልከት ለኢትዮጵያ ያደ



www.ethiopianorthodox.org

ረገውን መለኮታዊ ፍርድ በአንክሮ ፥ በምሥጋናና በቀና የአምልኮት መንፈስ በማድነቅ ፥ የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም አኗኗርና ብልጽግና በየአቅጣጫው የሚያደርገውን ሥር ነቀል ለውጥ ሁሉ በኃለና በማያቋርጥ የሀገርና የወገን ፍቅር ስሜት በመደገፍ ይህች የሰዎች ሁሉ ነፍስ ማረፊያና የኅሊና ፍርድ ሚዛን ማረፊያ የሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በተሐድሶ እንድትነሳ እምነቷን ሳይሆን አስተዳደሯን አሻሽላ ተደራጅታ ከእድፍ በነፃ መንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ በመጠመድ የተከታዮቿን ክርስቲያናዊና የቅድስና ኑሮ እንድትመራ በነበረው ምኞትና የጋለ ትክክለኛ የትግል ስሜት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት ጉባኤ ተመስርቶ በርካታ ስብሰባዎችን በማድረግ የቤተ ክርስቲያንን የተዘባ ሥጋዊና መንፈሳዊ አስተዳደር መርምሯል ።

እውነተኞች ልጆቿ ተባረው ሌቦችና አወናባጆች ያቆረቆዟትና የበዘበዟት መሆኑን በግል ጥቅም ምክንያት ጭቁን ካህናት ወጣቶችና ምዕመናን ተባብረው ስለ ቤተ ክርስቲያን ዕድገትና መሻሻል እንዳይሠሩ በገንዘብ ፥ በዘመድና በሥልጣን ኃይል እንዲከፋፈሉ መደረጉን ፥ የካህናትና የዲያቆናት ገቢ እጅግ አነስተኛ ስለሆነና በሕዝቡም ዘንድ ኑሮአቸው ከእለት ወደ እለት እየተናቀ በመሔዱ ፥ የቤተ ክርስቲያን ገቢ በመባከኑ ፥ የሕዝብ መሆኗ ተዘንግቶ የጥቂት ሰዎች መንደላቀቂያ ሆና የተሰጠች በማስመሰል ፍጹም ዓለማዊ ተግባር ሲካሔድባት ፥ የአስተዳደር በደል ሲፈጸምባት በማየት የተጣመመው አስተዳደር በፍጹም እንዲለወጥ ፥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከካህናት ፥ ከምዕመናንና ከወጣቶች በተውጣጡ መማክርቶች የሚመሩ የሥጋዊና የመንፈሳዊ ምክር ቤቶች እንዲኖሯት ፥ ሥልጣናቸውም በሕግ እንዲወሰን ፥ በቤተ ክርስቲያን አባቶች ፥ በካህናት ፥ በምዕመናንና በመንፈሳውያን ወጣቶች ድምፅ እንዲመረጡና ፥ ተመራጮች በመልካም ሥራቸው በንጽሕናቸው ፥ በቅድስናቸው በሕዝብ የተመሰከረላቸው ፈጽሞ የአድልዎ መንፈስ የሌላቸውና ለሕያው እግዚአብሔር የሚቆሙ ፥ ለወንጌል መስፋፋት የሚጥሩ ፥ ለሰው ልጅ እኩልነት ፥ ደኅንነት ነፃነት የሚጋደሉ ፥ ለእውነትም ሥራ የሚተጉ እንዲሆኑ ፥ በወንጌል ሥራ ከመድከም የሐዋርያነት ተልእኮአቸውን ከመፈጸም ሥልጣነ ክህነትና ቡራኬ ከመስጠት በስተቀር በሥጋዊ አስተዳደር ውስጥ ጨርሰው እንዳይገቡ ፥ የክርስቶስ ወንጌል ትምህርት በዘመናዊ ዘዴ እንዲደራጅ ፥የቤተ ክርስቲያን ንብረት እየተደራጀ በበጀት ለካህናትና ለዲያቆናት ኑሮ ማሻሻያ እንዲውል ፥ የቤተ ክርስቲያናችን ተከታዮች ፥ በሚገባ ተመዝግበው ተገቢው ትምህርት እንዲሰጣቸው ፥ ለዚህም የሬዲዮ ፥ ጣቢያ የማተሚያ ቤትና የተሟላ የሰባክያን ማሰልጠኛ እንዲቋቋምና የተባበሩ ሊቃውንት ተሰብስበው ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት በኅብረተሰብአዊነት መመሪያችን መሠረት እንዲሠሩ ፥ በመንፈሳዊ ቅናት ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚቃጠሉ ወጣቶች መመሪያቸውን አውጥተው እንዲደራጁ ማስፈለጉን ተቀዳሚ አላማው አድርጎ ታግሏል ።

ስለሆነም በሕያው እግዚአብሔር ፈቃድ በብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግልና በመለዮ ለባሹ ግንባር ቀደምትነት በተገኘው መብት ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ/ም በእምነታችን አንፃር ታሪካዊ ይዘት ባለው ድምፅ አሰጣጥ አባ መልአኩ ወ/ሚካኤል የአሁኑ አባታችን ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባት ሆነው መመረጥዎን በመንፈሳዊ ደስታ ተቀብለነዋል ። የተዘረዘሩት የትሩፋት ሥራዎችዎ ድንቅ ናቸው ። ሆኖም በውዳሴ ከንቱ ልንክብዎ አንሻም በትንሹ ታምነዋል ፥ የተቀበሉትንም ወርቅ አልቀበሩም አላዛጉም እንላለን በትልቁ ለመታመን ደግሞ ፥ የንዋይ፥ የጉሥዓ ፍቅር ሳያገብርዎ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን አደራ ሕዝቡም የጣለብዎትን የአባትነት ሥራ ያለመታከት እንደሚፈጽሙ እየተማመን ብዙ የምንጠብቅ መሆናችን እንገልጻለን ቤተ ክርስቲያን የሕዝበ ክርስቲያን በመሆኗ እንድትፀና እንዲያበረታቱ እንጠይቃለን ።

ሕያው እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን በሰላም ይጠብቅ አሜን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ወጣቶች በተሐድሶ ያላቸው ድርሻ ምንድነው ?

«ከድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ የተገኘ»
ከወጣቶች አጠቃላይ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ
ታዩ ብርሃን

በአንድ አገር ፤ በአንድ ቀበሌ ፤ በአንድ ቤተ ሰብ ፤ በአጠቃላይም በዓለም ውስጥ ሕያው እግዚአብሔር ሲዘነጋ ፤ ዓመፅ ይበዛል ሰዎች ከሥርዓት ውጭ ይሆናሉ ። ከሰብአዊ አቋማቸውም በላይ ይሆኑና ይታያሉ ። እውነትም በዋዛ ትደፈራለች ። ፍርድም ይዛባል ።ሰው በራሱ ይታበያል ። የሰውን እኩል ነት ፤ ነጻነትና ክብር ይዳፈራል ። ከዚህም የተነሣ አንዱ ገዥ ብዙው ተገዥ ፤ አንዱ ሀብታም ብዙው ችግረኛ ይሆናል ።

ፍቅር ይኮስሳል ። መተሳሰብ ይረሳል ። ሰው ወንጀለኛ ጨቋኝ ፤ አረመኔ ስግብግብ ሆዳም ይሆናል ። በንዋየ ፍቅር ፤ በወገን ጥላቻ የሠለጠነው ክፍል ድሆችን ይረግጣል ። አምላኩ ሆዱነውና በሕሠቃቂ መከራዎች ወገኖቹን ይቀጣል የግፍ ደም ሲሞላና ሲፈላ የእግዚአብሔር ፍርድ በየአገሩ ይገለጣል ። በዚህም ጊዜ የተደበለውና ሲረገጥ የኖረው ይነሣል ። ኃይልንም ያገኛል ። ሕያው ስሙን መጋረጃ አድርገው ሕዝቡን ያሠቃዩትን በቁጣው ይመታቸዋል ። ይህም ሐቅ በዘመናችን ተገልጧል ።

እንግዲህ ወንድሞች ሆይ! መጠራታችን ለከንቱ አይደለምና የሰማያዊት ሀገር የኢየሩሳሌም ምሳሌ የሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እንመልከት ። ከቅድስተ ቅዱሳት የተከበረው ዘለዓለማዊ የሕግ ጽላት ከእውነተኛው ሥርዓት ከወንጌል ሕግ ከነጠረው እምነታችን ሐዋርያት ፤ ቅዱሳን አባቶች ከደነገጉት ትክክለኛ ሥርዓት ውጭ ያለውን ሰዎች ለራሳቸው እንዲመች አድርገው የሠሩትን ጊዜ ያለፈበትን ብልሹ ወግ ፤ ነቀዝ የበላውን አድርባይነት ነፋስ የሚጠርገውን ወሬ ትርጉም የሌለውን አሉባልታ እናስወግድ ። በሃይማኖት አንድ የሆን ሁላችን በሥራ አንድ መሆንን እንወቅ ። እኛ ሌሎችን ስንወቅስ የሌሎች መዘበቻ እንዳንሆን እንጠንቀቅ ። ለሥራ መሰለፍ አለብን ። ዕቅድ መንደፍ አለብን ። ለቤተ ክርስቲያን የተሾመላትንና የተሾሙባትን እንወቅ ። የሚሠሩላት ንና የሚሠሩባትን እንለይ ። የሚጠቀሙባትንና የሚጠቅሚትን እንርዳ ። በከንቱ ሃይማኖት አለን እያልን መባከን የለብንም ። እኛነታችንን በሥራ የምንገልጽበት ወቅት አሁን ነው ። እጅ ለእጅ ተያይዘን ወንጌልን የምንሰብክበት ጊዜ አሁን ነው ። ችግረኞች ካህናትን የወሬ እንጀራ ከመመገብ የምንከላከልበትና ተጨባጭ ወደሆነ የሥራ ውጤት የምንመራበት ዘመን ይህ ነው የየግል መንገዳችንን ትተን በጋራ የምንጓዝበት ደቂቃ ቀርቧል ። በእጃችን ያለው ዕድል የአንድነታችን መሠረት ነው ። የሥራችን ፍሬ ነው ። ሀገራችን በሃይማኖት የተጠበቀችበትን ዘመናት ሁሉ ከቤተክርስቲያናችን ታሪክ እንረዳለን። እውነትን ፤ ሃይማኖትን ፤ ፍርድን በገንዘብ የሸጡ ሰዎች ከገቡባትና በአድርባይነታቸው ልወደቀው ሥርዓተ መንግሥት መሣሪያ ካደረጓት በኋላም ያለውን ታሪክ እናውቀዋለን ። ስለዚህ የተረገጠውን ጭቁን ክፍል በመንፈሳዊና በሥጋዊ አቋሙ እንዲጠናከርና ቤተ ክርስቲያንም ክብሯን ጠብቃ እንድትኖር ዛሬ ፊት የማይዞርበት የሥራ ትግል ፤ የሃይማኖት ጥራትና ጽናት ከወጣቶች ይጠበቃል ። ብልሹ የሆነ አስተዳደሯን በትክክለኛው መተካት የወጣቱ ምሁር አደራና ኃላፊነት ነው ። እንግዲህ እፎይታ ሠርቶ መሆኑን እንረዳ ፡ ታሪክ ይኑረን ።

የታሪክ ማኅደር ሲገለጥ ትንታኔው ብዙና ድንቅ ነው ። ረቂቅነው አሳዛኝ ነው ። አስደሳችም ነው ። በታሪክ መድረክ ላይ መውደቅ አለ ፤ መነሣት አለ ፤ መንሸራተት አለ ፤ ብዙ ድርጊቶች ይፈጸማሉ ። በሀገራችን ውስጥ በመካሔድ ላይ ያለውም አብዮት ታሪክ የወለደው ሐቅ ነው ። ረሃብ ፤ በሽታ ፤ ብርድ ጭቆና ፤ ግፍ ፤ ውርደት ፤ ወዘተ ለአብዮቱ መሠረት ሆኑ ። ይህ ብሔራዊ አብዮት ጭቁኖችን ሁሉ ስለሚያጠቃልል ፤ ወጣቶች ከምዕመናንና ከጭቁን ካህናት ጋር በመሠለፍ ትግላቸውን አፋፉሙ ። ብዙ ስብሰባዎችን አካሔዱ ። ብዙዎች እስከ መጨረሻው ቆመው ታገሉ ባይባልም ፤ አያሌ ዝንባሌዎች በታሪክ ዓምድ ላይ ይነበባሉ ። ዓላማ ፤ ትግልና ግብ የታሪክ ደም ፤ ሥጋና አጥንት ስለሆኑ ትንታኔውን ለዘመን እንተዋለን ።

ሆኖም ታሪክ ሲዘለል አጀማመሩ ለአዲስ ፤ መጭ ግራ ያገባልና ከማኅደር የተገኘውን በጥቂቱ ማስታወስ ጊዜን ማባከን አይሆንም ። በሕያው እግዚአብሔር ቸርነት ፤ በሰፊው ጭቁን ሕዝብ ኅብረት ፤ በመለዮ ለባሹ ግንባር ቀደምነት በኢትዮጵያ የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ በየአግጣጫው ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ በቀሰቀሰበት ወቅት ፤ በተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት አጠቃላይ ጉባኤ ተመሠረተ ። በርካታ ስብሰባዎችንም በማድረግ የቤተክርስቲያንን ሥጋ



www.ethiopianorthodox.org

# ወጣቶች በተሐድሶ ያላቸው ድርሻ ምንድነው ?

ዊና መንፈሳዊ አስተዳደር መረመረ ። የእውነተኞች ሊቃውንት ልጆቸ ጭቁን ካህናቶችና ወጣቶች ተባረው በምትካቸው የበዝባገሮችን መንሠራፋት አየ ። በምጣኔ ሀብት መሥመር ካህናት እጅግ የተናቁ መሆናቸውን ተረዳ ። ስለዚህም ይህ ሁሉ ተሻሽሎ ከለውጡ ጋር መደራጀት እንዳለበት ተገንዝቦ ባለአሥር ነጥብ ዓላማ አወጣ ። ከዓላማውም ጥቂቱ እየተፈጸመ ነው ።

ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበር አጠቃላይ ጉባኤን የካህናትንና የምዕመናን አጠቃላይ ጉባኤ የአንድነት ትግል በመመርመር ሥራው ቀናና የተስተካከለ ይሆን ዘንድ ፤ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጊዜያዊ ጉባኤን በሕግ አቋቋመልን ። በጣምም ደስ የሚያሰኙ ርምጃዎች ተወስደዋል ፤ እየተወሰዱም ናቸው ።

የስብሰባችን መሠረት ፤ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ እምነታችን ናት ። ስለዚህም ስለቤተ ክርስቲያን የወደፊት ዕድልና አቋም መርምሮ መሠረቷን ለማጽናት የቀሳውስትን የኑሮ ሁኔታ ለማስተካከል ራሳችንን በተጨባጭ ድርጊቶች ከቤተክርስቲያን ጋር ለማዋሐድ ምዕመናንን በትምህርተ ወንጌል ለማነጽ ቤተ ክርስቲያንን ከቀሳውስት ፤ ከምዕመናን ከወጣቶች በተውጣጣ ድርጅትና ከአለችበት ከባድ የአስተዳደር ጉድለት ለማላቀቅ ቤተክርስቲያን ሊኖራት የሚገባውን የምጣኔ ሀብት ምንጭ ለመን ደፍና በአስቸኳይ በሥራ ላይ ለማዋል በሥነ ጥበብ፤ በሥነ ጽሑፍ ና በሥነ ምግባር የታነጹ ትውልድ እንዲኖራት ለማድረግ ሊቃውንት መጻሕፍትን አደራጅተው ፤ ለታሪክና ለ ት ው ል ድ እ ን ዲ ያ ቆ ዩ ለማድረግ የሥራ መስኮችን በአፋጣኝ ለመክፈትና በአጠቃላይም ዓላማችንን በሥራ ለመተርጐም ሲሆን ፤ ለዚህ ሁሉ የመንፈሳውያን ወጣቶች መመሪያ ወጥቶ ተገቢው ሥራ እንዲከናወን የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ፤ እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ጊዜያዊ ጉባኤ አስፈላጊውን ርዳታና ትብብር እንዲያደርጉልን በቤተ ክርስቲያን ስም እንጠይቃለን ።

እንግዲህ ወጣቶች ሆይ ! ይህ ሁሉ በወሬ አይገኝም ። በስብሰባ ብዛት ብቻ አይፈታም ። ከውጭ ሆኖ በማማት አይቃለልም ። በይሉኝታም አይተውም ። ፍጹም የሆነ ትግል መንፈሳዊ ተጋድሎ ይደረግበታል እንጂ እኛ ወጣቶች አንድነታችን በሃይማኖታችን ፤ በሥራና በማንኛውም ተጨባጭ በሆነ መንፈሳዊ ሐቅ የጸና ይሆናል ። የጭቁን ካህናት ፤ የምዕመናንና የወጣቶች ፍጹም የሆነ የእኩልነትና የአንድነት ትግል ያሸንፋል ። ድል የሰፊው ሕዝብ ነው።«በክርስቶስ ቸርነት ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ጋር ትቅደም»

# ከክርስቲያናዊ ተራድኦ ጽ|ቤት የተገኘ

## የግእዝ መጻሕፍት ትርጉም ፕሮጄ

### የ ፕ ሮ ጄ ው ዓ ላ ማ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የብዙ መቶ ዓመታት ታሪክ ውስጥ በርከት ያሉ መንፈሳውያን አባቶችንና ምሁራንን በብዙ የመንፈሳዊ ትምህርት ቅርንጫፎች አፍርታለች ። እነዚህ ምሁራን እንደ ብሉይ ኪዳን ፡ አዲስ ኪዳን ፡ የመሳሰሉት ትርጉሞችና ልዩ ልዩ መጻሕፍቶችን በእጅ ጽሑፍ አበርክተዋል ። እነዚህ መጻሕፍት በቂ ወይም ምንም ኮፒ የሌላቸው ከመሆናቸውም በላይ ከጊዜ ብዛትና ከአያያዝ ጉድለት ሊበላሹ እንደሚችሉና የተበላሹም ወይም የተቃጠሉም እንደሚኖሩ አይጠረጠርም ። ይህም ሆኖ የአብዛኛው የሊቃውንቱ ጽሑፍ ያለው በግእዝ በመሆኑ አሳባቸው ለሌላው ሕዝብ አይተላለፍም ። ስለሆነም የግእዝ ትርጉም መጻሕፍት ፕሮጄ እንዲዘጋጅ አስፈልጓል ።

ባጭሩ የትርጉም መጻሕፍት ፕሮጄ በጥፋት አፋፍ ያሉትን መጻሕፍት ለማዳን ኮፒ የሌላቸው በርካታ ኮፒ እንዲኖራቸው ማድረግና ምእመናን በሚረዱት ቋንቋ ለምእመናን ማቅረብ ነው ። ለፕሮጀክቱ የተገኘው ገንዘብ ፸፯ሺህ ፩፻፷ ብር ከ፷፯ ሣንቲም (ስድሳ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ስድሳ ብር ከሃያ ስድስት ሳንቲም) ሲሆን ፡ መ/ ቤቱ በሚያሳትማቸው መጻሕፍት ላይ ትርፍ አይፈልግም ። መጽሐፉን ለማሳተም የወጣው ገንዘብ ታስቦ መጽሐፉ በዋናው ብቻ ተሸጦ ገንዘቡ ገቢ ከሆነ በኋላ ሌላ መጽሐፍ እንዲታተምበት ይደረጋል ።

## የአኵስም እደ ጥበብ ሥራ ድርጅት

### ዓላማውና አጀማመሩ

የአኵስም ከተማ ጥንት ረዘም ላለ ጊዜ የኢትዮጵያ ነገሥታት ዋና ከተማ ሆና በመቆየቷ በዚህች ሀገር ውስጥ ከፍተኛ የታሪክ ቦታ ከሚባሉት አንደኛዋ ነች ። ብዙ የዘመኑ ምሁራንና የእደ ጥበብ ሥራ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ኖረውባታል ። በርከት ያሉ ልዩ ልዩ ታሪካዊ ቅርሳቅርሶችም ይገኙባታል ። በዱሮ ዘመን በከተማዋና በአካባቢዋ የኖሩት ሕዝቦች በቅብ ሥዕል ፡ በብራና ጽሑፍ፡ በጥልፍ፡ በሸክላ ሥራ ፡ በብርና በወርቅ ሥራ ፡ በእንጨትና በድንጋይ ሥራ ፡ በሸማ ሥራ ይህንና ይህን በመሳሰሉት የእጅ ሙያዎች በጣም የታወቁ ነበሩ። ባሁኑ ጊዜም በአኵስምና በአካባቢዋ የሚኖሩ በርካታ ሰዎች ሙያውን ከአባቶቻቸው ወርሰው በዚሁ ሙያ በመተዳደር ላይ ይገኛሉ ። የአኵስም ከተማ ጥንታዊነትና ታሪካዊነት የቱሪስት መሳቢያ አድርጓታል ። ስለሆነም ሰዎቹን በማሳመን በማስተባበርና በማደራጀት ዕቃዎችንና ሙያቸውን በማሻሻል የተሻለ ምርት ለገበያ ለማቅረብ በመቻል ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ የነበረው ጥንታዊና ታሪካዊ ቅርጻ ቅርጾችም እንዳይጠፉ የአኵስም እደ ጥበብ ሥራ ድርጅትን ማቋቋም አስፈለገ ።

## የአባ ሰላማ ከሣቴ

### ብርሃን ማተሚያ ቤት

#### ሀ. ዓላማው

የአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ማተሚያ ቤት እንዲቋቋም ያስፈለገበት ምክንያት ሐረርጌ የልዩ ልዩ ሃይማኖት ተከታይ የሚበዛበት ክፍለ ሀገር በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ለማስፋፋትና በማኅበራዊ ኑሮ ችግር ያለባቸውን በተለይም የሙትልጆች ለመርዳት ነው ። ይሁን እንጂ እላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ማተሚያ ቤቱ ዓላማውን ማሟላቱ ቀርቶ ለሠራተኞችም ደመወዝ መክፈል አልፎ አልፎ ይቸግረው ነበር ። ስለሆነም እንደገና በአዲስ ሁኔታ ማቋቋም ስላስፈለገ ፕሮጄ ተዘጋጅቶ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ ተጠየቀና ሃምሳ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ ብር ተገኘ ። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ገንዘቡን ከፍሎ የጨረሰው በሦስት ዓመት በሦስት ክፍያ



www.ethiopianorthodox.org

በመሆኑ የመጨረሻው ክፍያ የተፈጸመው ከአንድ ወር በፊት ነው ።

በተገኘው ርዳታ ዘመናዊ የማተሚያ ቤት መኪናዎች ከጀርመን አገር በማስመጣት አሮጌዎቹን ተክተናቸዋል ። የተረፈውም ለመቋቋሚያቸው ሆነ። ዛሬ የማተሚያ ቤቱ የአሠራር ሁኔታ ሁሉ ተሻሽሎ የሙት ልጆችን በማሳደግና በማስተማር ላይ ይገኛል ።

# የሐረር ሕፃናት ማሳደጊያ

## ዓላማውና አመሠራረቱ

ይህ የችግረኞች ልጆች ማሳደጊያና ማስተማሪያ ት/ቤት ከተቋቋመ ዐሥራ አንደኛውን ወር ይዟል ። ዓላማው በልዩ ልዩ ምክንያት በተለይም ድርቅ ባስነሣው ችግር የተነሣ መግቢያ ያጡትን ልጆች ሰብስቦ እንደ ደብረ ማርቆስ ት/ቤት በአዳሪነት እያኖረ በመጠኑ መንፈሳዊውንና ዘመናዊውን ትምህርት እየሰጠ ማሳደግ ነው ። ድርጅቱን የሚረዳው ኪንደርኖት ሂልፌ የተባለ ጀርመናዊ ርዳታ ሰጭ ድርጅት ሲሆን በክርስቲያናዊ ተራድኦ ጽ/ቤት ሥር የማሳደጊያው የበላይ ተጠባባቂ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የሐረርጌ ሊቀ ጳጳስ ናቸው ። ይህ ድርጅት በሐረር ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ሒሳብ ከፍቶ ሒሳቡ በቀጥታ ከርዳታ ሰጭ ድርጅት ይላክለት ጀምሮአል ። ይህም ለአሠራራችን የሚያመችን ስለሆነ የመረጥነው መንገድ ነው ።

# የደብረ ማርቆስ ችግረኛ

## ልጆች መርጃና ማስተባበሪያ

በደብረ ማርቆስ የችግረኞች ልጆች መርጃና ማስተማሪያ ት/ቤት ከተቋቋመ ገና አንድ ዓመቱ ነው ። የዚህ ት/ቤት ዓላማው እጅግ በጣም ችግረኞች ከሆኑ ቤተ ሰብ የሚወለዱትን ልጆች ከመላው ክፍለ ሀገር ሰብስቦ በአዳሪነት ት/ ቤት እያበላና እያለበሰ ልጆቹ ሥድስተኛ ክፍል እስኪደርሱ ድረስ ዘመናዊውን ትምህርትና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በማጣመር ማስተማር ነው ። በቤተ ክርስቲያን በኩል ት/ቤቱ የሚሰጣቸው የትምህርት ዓይነቶች ቅኔና ጽዋትወ ዜማ ፡ ትርጓሜ መጻሕፍት ፡ የመጽሐፍ ቅዱስና የስብከት ዘዴ ናቸው ። አዳሪ ት/ቤት እንደመሆኑ መጠን ሕንፃው አስፈላጊዎቹን ክፍሎች በሙሉ ይዟል ። ሕንፃውንም በርዳታ ሰጭዎቹ ገንዘብ ያሠራነው እኛም ስንሆን የፈጀው ፩፻፹፯ሺ የኢትዮጵያ ብር ገደማ ነው ። ባሁኑ ጊዜ ድርጅቱ ፩፻፳ ሕፃናትን ተቀብሎ በማስተማርና በማሳደግ ላይ ይገኛል ። ዛሬ ት/ቤቱ በቦርድ ይተዳደራል ። ከርዳታ ሰጭው የሚላከውም ገንዘብ በቀጥታ ደብረ ማርቆስ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ይገባል ።

# በሲዳሞ የተደረገ ጊዜያዊና

## ዘለቄታ ርዳታ

## ዓላማውና አጀማመሩ

ሀ፡ የቀድሞው መንግሥት ስለ ረኃብ እጅግም ባልተጨነቀበት ጊዜ በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ረኃብ መግባቱን ከአንዳንድ ሰዎች እንደሰማን በተቻላቸው መጠን በአስቸኳይ ርዳታ እንዲደረግልን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጽ/ቤት በቴሌግራም ተጠይቆ ለጊዜው አስቸኳይ ርዳታ ከስዊስ ዲያሪ ፕሮዳክት ፪ሺ፸፰ ኪሎ ክራም የዱቄት ወተት ተልኮልን ይህንኑ በርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን መኪና በመጠቀም ከካህናት ማሠልጠኛው ሠልጥነው በወጡት ሁለት ዲያቆናትና በምክትል የአውራጃው አስተዳዳሪ አማካይነት ለተጎዱት ዘላኖች እንዲደርስልን አድርገናል ። በርግጥም መድረሱ በተላከልን ሪፖርት ተረጋግጧል ።

ሆኖም በትራንስፖርት በኩል ችግር ገጥሞን ነበር።

ለ፡ ዘለቄታ ያልኩት አዲሱ የውሃ ጉድጓድ ማስቆፈርና የነበሩትን ምንጮችም ጭምር ለማስጠረግ አቅደን ከውሃ ሀብት ልማት ጋር በመተባበር ለመሥራት ስንሞክር ከበድ ያለ ገንዘብ የሚጠይቅ ሆኖ ስለተገኘ በቦረና አውራጃ በነገሌ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ የውኃ ኩሬ እንዲቆፈር ከሕዝቡ ሦስት ሺህ ብር ከልማት ኮሚሽን ፱ሺህ ብር በድምሩ ፲፪ሺህ ብር ወጭ ተደርጓል። የተቆፈረውን የውኃ ጉድጓድ ለመጐብኘት ባያደርስንም በአፈጻጸሙ ከካህናት ማሠልጠኛችን ተመርቀው በወጡት በቀሲስ መዘምር ማሞ ላይ እምነት አለን ።

በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም ለወሎና ለትግሬ የተሰጠ ርዳታ፡

ዓላማውና አጀማመሩ ፤

፩/ በወሎ ከፍተኛ ችግር መኖሩን ከማንም በፊት ለዓለም ያሰማው የክርስቲያናዊ ተራድኦ ጽ/ቤት ነው ። የወሎ ሕዝብ እየተሰደደ መምጣት ሲጀምር የክርስቲያናዊ ተራድኦ ጽ/ቤት በአስቸኳይ ችግሩን በቴሌግራም ለርዳታ ሰጭዎች በማሳወቅና በየጊዜው አጥኚ ቡድን ወደ ሥፍራው በመላክ «መና ለዓለም ከተባለው የጀርመን ድርጅት ፩፻፸ሺህ ብር ርዳታ አግኝቶ ለችግሩ ማቃለያ እንዲውል በቤተ ክር



www.ethiopianorthodox.org

ስቲያኑ ስም በጊዜው ለነበሩት የርዳታ ማስተ ባበሪያ ኮሚሽን ኃላፊ አስረክቧል ። ይህም ግንቦት ፱ ቀን ፳፰ ዓ/ም በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ተብራርቶ ተገልጿል ።

፪/ ትግራይ ፥ በትግራይም ተመሳሳይ ችግር በመ ኖሩ ፪ሺህ ፭፻ ብር ለችግሩ ማቃለያ እንዲውል ሆኖኗል ።

ከዚህ በላይ የተሰጠው ርዳታ ለጊዜው የሚ ጠቅም እንጂ ለችግሩ ዘለቄታ መፍትሔ የማ ይሆን በመሆኑ በመንግሥት ላይ የወደቀውን ሸክም ለመርዳት ከመንግሥቱ ጋር በመተባ በር ጊዜያዊ መጠለያ ለማቋቋም ሰዎቹም እን ደገና የፈረሰ ቤታቸውን እንዲያቋቁሙ በደንብ የተጠኑ ፕሮጄዎችን አዘጋጅቷል ።

ልዩ ልዩ አትክልቶችንና ዛፎችን፥መጋቢ መን ገዶችን፥መጋዘኖችን፥ለሕዝቡ ለመሥራት ዕቅድ ነበረው፤ይሁን እንጂ የሥራው ከባድነት ጽ/ቤቱ ካለው የሰው ጉልበት ጋር የማይመጣጠን ሆኖ በመገኘቱ የታለመው ከፍጻሜ ሳይደ ርስ ቀርቷል ።

## የጋምቤላ አውራጃ ረኃብ በ፲፱፻፳፫ ዓ/ም

በ፲፱፻፳፫ ዓ/ም በኢሉባቦር ክፍለ ሀገር በጋም ቤላ አውራጃ በክረምቱ ከፍተኛ የውኃ መጥለቅለቅ የተነሣ ከ፳ሺህ በላይ የሆኑ ሰዎች ሰብል ተበላሽቶ ረኃብ ገብቶ ነበር ። ይህንኑ የክርስቲያናዊ ተራድኦ ጽ/ቤት እንደተረዳ በተጠቀሰው ዓ/ም መጀመሪያ ላይ ፳፻ ኩንታል ባቄላ ገዝቶ በአውራጃው አስተ ዳዳሪ አማካይነት ለሕዝቡ እንዲታደል ከማድረ ጉም በላይ በካሽ ፫ሺህ ፭፻፳ ብር ሰጥቷል ። በጠቅላላው በጋምቤላ ደርሶ የነበረውን ረኃብ ለማ ስታገሥ ለተገዛው እህል ማመላለሻ ጭምር ፳፭ሺህ የኢትዮጵያ ብር በርዳታ ተገኝቶ ወጭ ሆኗል ።

እ - ኤ - አ - በ፲፱፻፸፬ ዓ/ም የካህናት ችሎታ

## ማሻሻያ ኮርስ ስለመስጠት

ይህ የካህናት ችሎታ ማሻሻያ ኮርስ ዓላማ ቀደም ሲል የተገለጸ በመሆኑ አሁን መድገም የሚ ያሻው አይመስለኝም ።

የካህናት ችሎታ ማሻሻያ ኮርስ ለሦስተኛ ጊዜ እ - ኤ - አ - በ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ስለሚሰጥበት እኳኋን እኔ አቶ ንዋይ ወልደ ጻድቅና አቶ ኃይሉ በየነ ሆነን በሚገባ አጥንተን ነበር ።

ኮርሱ ሊሰጥ የታቀደው በአውራጃና ወረዳ ደረጃ ላሉት ሊቃነ ካህናትና በአውራጃና ክፍለ ሀገር ደረጃ ላሉት ለቤት ክህነት ሥራ አስኪያጆች የኮርሱ ተካ ፋዮች ከፍተኛ ቊጥር ፯፻፷፰ ሰዎች ሲሆን ይህን ያህል ሰው በአንድ ጊዜ ለማስተናገድ ስለሚያስቸ ግርና በሥልጣንም በጣም የሚለያዩትን ሰዎች አንድ ላይ ሆናችሁ ተማሩ ማለቱ በተለይም ከካህናት በኩል ተቃውሞን ሊያስከትል ስለሚችል ኮርሱ በተለያዩ ጊዜያትና ለተለያዩ ሰዎች እንዲሰጥ ሆኗል።

ሀ/ ሥራ አስኪያጆች እዚህ በሚቆዩበት ጊዜ ሥራው እንዳይበደል በማሰብ ፥

ለ/ የክፍለ ሀገር ቤት ክህነት ሥራ አስኪ ያጆች ኮርስ እንዳበቃ በአውራጃ ደረጃ ላሉት የሥራ አስኪያጆች ለሃያ ቀን እንዲሰጥ ፥

ሐ/ በወረዳና አውራጃ ደረጃ ላሉት ሊቀ ካህናት ደግሞ ለ፴ ቀናት ያህል እንዲ ሰጥ ተመድቧል ። የሚሰጡት የትም ህርት ዓይነቶችና ጠቅላላ የኮርሱ አሰ ጣጥ ሁኔታ በዝርዝር ተጠንቶ ለኮርሰኞቹ የመጓ ጓዣ ፥ የምግብ ፥ የሕክምና ፤ የመኝታና ለአስጠኚ ዎቹ አበል ጭምር ወጭው ፩፻ ፵፰ሺህ ፬፻፬ ከ፹ ሣንቲም በመሆኑና ይህም ለችሎታ ማሻሻያ ኮርስ ከርዳታ ሰጭዎች ተሰጥቶ በእጅ ከቀረው ገንዘብ በላይ በመሆኑ የኮርሱ ዝግጅት እንደ ተጀመረ ተሠረዘ ። የሰበካ አስተዳደር ደንብን ለማቋቋም የመ ጣው ገንዘብ በመገባደዱ ለካህናት ችሎታ ማሻሻያ ኮርስ መጥቶ ተሠርቶበት የተረፈው ገንዘብ ለሰበካ አስተዳደር ደንብ ማቋቋሚያ እንዲውል ተደረገ ።

## በኩናማ የሻምቡ ት|ቤት ሥራ ዕቅድ

## (ከ፲፱፻፶፯ - ፲፱፻፶፱ ዓ|ም )

ኩናማ የተባሉት ጎሣዎች የሚኖሩት በኤር ትራ ክፍለ ሀገር በምዕራባዊ ክፍል በሱዳን ጠረፍ አቅራቢያ ነው ። በዚህ ወረዳ በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም ፲፻ሺ ሰዎች ይኖሩ እንደ ነበር ታውቋል ። የወረዳው ሕዝብ የራሱ ባህል ያለው ሲሆን አብዛኛው ሕዝብ ልማዳዊ አምልኮት አለው ። በእምነት በኩል ጥቂቱ እስላም በጣም ጥቂቱ ደግሞ ክርስቲያን ነው ።

በኩናማ ወረዳ ከአሥመራ ፫፻ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሻምበቆ በምትባል ሥፍራ ማኅበረ ሐዋርያት የተባለ አንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ማኅበር ተቋቋሞ ሥራ ውን ሲያካሂድ ቆይቷል ። ይህ ማኅበር እስከ ፲፱፻፶፮ ዓ/ም አንስተኛ ት/ቤቶችን ክሊኒኮችንና ሁለት ዘመናዊ የእህል ወፍጮዎችን አቋቁሞ ሕዝቡን ሲያገለግል ቆይቷል ።



www.ethiopianorthodox.org

# የቅዱስ ጳውሎስን ሆስፒታል አገልግሎት ማስፋፋት

የቅዱስ ጳውሎስን ሆስፒታል ማንኛችንም እና ውቀዋለን ። ይህ ሆስፒታል በተለይ ድኖች የሚታከሙበት የበጎ አድራጎት ሆስፒታል የነበረ መሆኑ ይታወቃል ።

እ - አ - አ - ከ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በፊት በሆስፒታሉ ተኝተው ለሚታከሙ ለ፻፷ ሕሙማን ብቻ አልጋ ሲኖር በነበረው አነስተኛ ድርጅት የተነሳ ፺ሺህ ያህል ተመላላሽና ከ፫ሺህ እስከ ፯ሺህ ፭፻ የሚተኙ ሕመምተኞችን ብቻ በዓመት ያክም ነበር ።

ይህ የአገልግሎት መጠን በነፃ እንዲታከሙ ኑሮአቸው ለሚያስገድዳቸው ሰዎች በቂ ባለመሆኑ ሆስፒታሉ ተስፋፍቶ ከ፺ሺ እስከ ፷ሺ ተመላላሾችና ከ፴ ሺህ ፭፻ እስከ ፭ሺህ የሚተኙ በሽተኞችን ባመት ለማከም እንዲችል በበጎ አድራጎት በኩል ፕሮገፔ ተዘጋጅቶ ለክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚቴ ቀረበ ። ሆስፒታሉ ቀድሞ ከነበረበት ቦታ ተነሥቶ ወደ ሌላ እንዲዛወር የተደረገበትም ሌላው ምክንያት ሕመምተኞች የመንፈስ ዕረፍት ሊያገኙ በሚችሉበት ቦታ የተሠራ በመሆኑም ጭምር ነው ።

የሆስፒታሉ ዕቅድ ለክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚቴ ቀርቦ ኮሚቴው ካመነበት በኋላ ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጽ/ቤት እንዲተላለፍ አድርጓል።

## በልዩ ልዩ ምክንያት በጅምር የቀሩ ዕቅዶች ፡

፩፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ

### ዓላማው

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የብዙ መቶ ዘመናት ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ ተለይቶ ሊታይ የማይችል ነው ። የሀገሪቱን ታሪክ የጻፉና ለመጻፍ የሞከሩ ሁሉ ሳይወዱ በግድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስንም ታሪክ ጽፈዋል ። ስለሆነም በግእዝና በውጭ አገር ቋንቋ የተጻፉትን መጻሕፍት ከየገዳማቱና ከሌላም ቦታ ሰብስቦ ወደ አማርኛ ለመተርጐምና በአንድ መጽሐፍ ጠርዞ በማሳተም ለምዕመናን ለማቅረብና የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለማሳወቅ ነው ። መጻሕፍትን ከየገዳማቱና ከሌሎች ቦታዎችም ሰብስቦ ተርጉሞ ለማሳተም የተፈለገው ገንዘብ ፷ሺህ፪፻፺፱ ብር ከ፲ ሳ/ ነበር ።

## ፪ የሰበታ ቤተ ደናግል

ትንደ ምግባረ ሠናይ ፡ እንደ ደብረ ማርቆስ መንፈሳዊ ት/ቤትና እንደ ሐረር ሕፃናት ማሳደጊያ ሁሉ በሰበታ ያለውን ቤተ ደናግል ለመርዳትና ልዩ ልዩ የእጅ ሥራ ትምህርት ለማስተማር ጥረት ተደርጎ ነበር ። ዳሩ ግን የተጠየቀው የርዳታ ሰጭ ድርጅት የመንኰሳት ዕድሜ ሊደግፋቸው ከሚችለው የዕድሜ ክልል ውጭ በመሆኑ ቀርቷል ።

፫፡ እ . ኤ . አ . በኮልፌ የቅዱስ ጳውሎስ ክሊኒክ(፲፱፻፸፩—፲፱፻፸፪)

## ዓላማውና አጀማመሩ

በኢትዮጵያ የዓይንና የጥርስ ሐኪሞች እጥረት መኖሩ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከመረጋገጡም በላይ በየገጠሩ የሕክምና መድኃኒቶች እጥረት ስላለ ይህንኑ ለማቃለል ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ክሊኒኮች እንዲቋቋሙ አስፈለገ ።

ስለሆነም በኮልፌ ቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት ቅጥር ግቢ አንድ አከፋፋይ ክሊኒክና በአሥራ አራቱም ክፍለ ሀገሮች ቅርንጫፍ ክሊኒኮች እንዲቋቋሙ ታቅዶ በመጀመሪያ አከፋፋይ ክሊኒኩን የማቋቋም ርምጃ መውሰድ ተጀመረ ። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም የአስፈላጊ ዕቃዎችን ዝርዝር ዋጋ እንዲሰጥ ተጠይቆ ሰጠና በዚሁ መሠረት $ 2833.37 ሣ/ ለዕቃዎቹ መግዣ«መና ለዓለም»ከተባለው ድርጅት ተላከልን ። እኔ ሥራውን እስከጀመርኩበት ጊዜ ድረስ ለክሊኒክ የመጣው ገንዘብ $ 3544.83 ሣ/ ሲደርስ ምንም ሥራ አልተጀመረበት ነበርና የፕሮገፔው ጉዳይ እንደገና ተቀስቅሶ ባለው ገንዘብ የመመርመሪያ ክፍል የሕመምተኞች መቆያ ክፍል



www.ethiopianorthodox.org

የመድኃኒት መሸጫ ክፍልና እንዲሁም ለየክፍ
ሎቹ በሮች ተሠሩ ።

የውጪ በረንዳ በድንጋይ ተነጠፈ ። ለሐኪ
ሞቹ ለወንድና ሴት ሕመምተኞችም የሽንት ቤቶ
ችና መታጠቢያዎች ሕንፃ ሥራ በታወቁ መሐን
ዲሶች ተዘጋጀ ። ዳሩ ግን ከ$ 3544.83 ሣ/ የተረፈን
$ 544.33 ሣ/ብቻ በመሆኑ የክሊኒኩን ሥራ ማስጨ
ረስ አልተቻለም ። ስለሆነም ተጨማሪ ርዳታ የሚ
ያስፈልግ መሆኑ«ለመና ለዓለም»ቢገለጽለትም ርዳታ
ሰጭው ለክሊኒኩ ከዚህ በላይ ርዳታ ለመስጠት
ባለመፍቀዱ አከፋፋይ ክሊኒክ በአዲስ አበባ ለማ
ሠራት የታቀደው ዕቅድ ተጨናገፈ ።

ይሁን እንጂ በጣም ውድ የሆኑ የሕክምና
መሣሪያዎችና መድኃኒቶች ከአንድ አባል ቤተ ክር
ስቲያን ለቅዱስ ጳውሎስ ክሊኒክ ተልኮ ስለ
ነበር በትርፍ ጊዜያቸው የት/ቤቱን ተማሪዎች በካ
ህናት ማሠልጠኛ የሚማሩትን ካህናትና ያካባቢ
ውን ሕዝብ እንዲያክሙበት በትርፍ ጊዜያቸው
የሚሠሩ ሦስት በጎ ፈቃደኞች ዶክተሮችን አግኝ
ተን ሥራውን ለማስጀመር ስንጓጓ ለሽንት ቤቶቹ
ማሠሪያ ገንዘብ ሊገኝ ስላልተቻለ የመጣውን የሕ
ክምና መሣሪያ፥ መድኃኒቶች የቤተ ክህነት ቅጥረኛ
የሆኑት የት/ቤቱ ድሬሰር እንዲጠቀሙበት ሰጥተ
ናቸዋል ። ይሁን እንጂ አሁንም ክሊኒኩን ለማስ
ጨረስ $ 8500 ገንዘብ ካገኘን በዕቅዳችን እንገፋ
በታለን ።

## ፬፡ መተከል ቡለን ት/ቤት

ቡለን የሚባለው ሥፍራ የሚገኘው በጎጃም
ክፍለ ሀገር በመተከል አውራጃ በወንበራ ወረዳ
ወደ ሱዳን ጠረፍ አቅራቢያ ነው ። በዚህ ተራራማና
ቀና መንገድ በሌለው ሥፍራ ሻንቅላ ሽናሽና ኦሮሞ
የተባሉ ጐሣዎች ይኖሩበታል ። እነዚህ ሦስቱም
ጐሣዎች ከአባቶቻቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ልማ
ዳዊ አምልኮ ያመልካሉ ። ጥቂቶቹም የተለያየ ሃይ
ማኖት ተከታዮች ናቸው ። አልፎ አልፎም አንዱ
በሌላው ላይ ጦርነት ያደርጋል ። ስለሆነም የኢ
ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ድር
ጅት ፩/ የክርስቲያንን እምነት ለማስፋፋት ፪/ ጐሣ
ዎቹን ለማግባባትና ሰፊ የማኅበራዊ ኑሮ አገልግ
ሎትን ለመስጠት ጥረት ያደርግ ነበር ።

ይኸው ድርጅት ከጭቃ የተሠሩ የሁለት ክፍ
ሎች ት/ቤት አቋቁሞ በሦስት ካህናት አማካይ
ነት ከ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ጀምሮ ለሦስት ዓመት ትምህ
ርት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ የተማሪዎቹ ቁጥር እየጨ
መረ በመሄድና ከእንጨት የተሠራውም ቤት ምሥጥ
ስለሚበላውና ዕድሜ ስለማይኖረው ት/ቤቱ ተስፋ
ፍቶ እንዲሠራለት ለክርስቲያናዊ ተራድኦ ጽ/ቤት
አመለከተ ። በዚህ ቀበሌ ሐዋርያዊው ድርጅት
ከሚሰጠው ትምህርት በቀር ሌላ ምንም ዓይነት
ት/ቤት አልተቋቋመም ነበር ።

ባካባቢው አልፎ አልፎ በሚነሣው ተላላፊ
በሽታ የተነሣ የቀይ መስቀል ርዳታ እንዲሰጥ የሚ
ያሳስበውም ይኸው ድርጅት ነበር ። በዚህ ምክንያት
አልፎ አልፎ የልብስና የምግብ ርዳታም በተለይ
ለተማሪዎቹ ይደረግላቸው ነበር ።

የት/ቤቱ መስፋፋት ዕቅድ በክርስቲያናዊ ተራ
ድኦ ጽ/ቤት በሚገባ ከተጠና በኋላ ፕሮጀው ለዓ
ለም አብያተ ክርስቲያናት ጽ/ቤት ቀርቦ ከርዳታ
ሰጭዎቹ የተፈለገው ፲ሺህ ብር ተፈቅዶ በተለያዩ
ጊዜያት ወደዚሁ ተላከ።የመጀመሪያው የ $4.744.50
ሣንቲም እንደደረሰም ወደ ት/ቤቱ እንዲተላለፍ ተደ
ረገ ። በዚሁ ጊዜ ሐዋርያዊው ድርጅት ከተ
ፈለጉት ሥድስት ክፍሎች ውስጥ አምስ
ቱን ለማሠራት ችሏል ። ይሁን እንጂ አሠራሩ የክ
ርስቲያናዊ ተራድኦ ካዘጋጀው ፕላን ውጭ በመ
ሆኑ ተራፊውን ገንዘብ $ 6.557.20 ሣንቲም ማስተላ
ለፋች ግር ፈጥሮ እስከ ሰኔ ወር ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ጽ/ቤቱ
በጉዳዩ ከት/ቤቱ ኃላፊና ከቅድስት ሥላሴ ካቴድ
ራል ጋር ሲጻጻፍበት ቆይቷል ። በኛ በኩል በአ
ካባቢው ምሥጥ በብዛት ስላለ ከእንጨትና ከጭቃ
የሚሠራ ቤት ዕድሜ የማይኖረው መሆኑን ተረ
ድተን የድንጋይ ቤት እንዲሠራ ዕቅድ እንዲወጣ
ሆነ ። ዛሬም እኛ የምንለው በሕዝቡ በኩል የሚ
ዋጣው ገንዘብ ስብሰባ ከተጠናቀቀ ፥ ከዚህ ቀደም
ላስተላለፍነው ገንዘብ ሪፖርት ከቀረበ ፥ ስለ ት/
ቤቱም የሕንፃ ሥራ ት/ቤቱ ከመሐንዲሶች ጋር
የተፈራረመበት የውል ፎቶ ኮፒ ከተላከልን ቀሪ
ውን ገንዘብ $ 6557.20 ሣንቲም እናስተላልፋለን ።



www.ethiopianorthodox.org

የ፫ኛው ፓትርያርክ በዓለ ሢመት

# ስለብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የፓትርያርክነት ታሪካዊ ምርጫ የተደረሱ ቅኔዎችና ግጥሞች

መወድስ ቅኔ ከአበባው ይግዛው

ትንቢተ ድንግል ፈክር ተክለ ሃይማኖት
በዘተዓብዮ ነፍስከ ለእግዚአብሔር መድኅን
ርእሰ ማዕዘንተ እምኮነተ ለሕንጻ መለኮት ሥልጣን
ነደቅት ዘይሜንንዋ አስኬማከ ዕብን ፤
እንዘ ዕራቆሙ ለብዑላን
አኮኑ አጽገበ እምበረከቱ ለርኁባን ፤

ለ ዓ ለ ም

ንግርሂ ምሕረቶ ለእግዚአ ሐዲስ ዘመን
እምድኅረ ሰበረ ወቀጥቀጠ መናሥግተ ዘሐጺን።
በወላይታ ቅድስት ደብረ ሕያዋን
ሥርዐተ ክህነት ቅኔ ደብተራ አምጣነ ተተክለ
ለጻድቃን ።

** ** **

የግዕዝና የአማርኛ ታሪካዊ ቅኔ ።

ከመሪጌታ ሣህለ ማርያም ዋጋው

ጥበብ ወሕግ ለእመ ተውህቦ
ለመልአከ ኃይል ሰሎሞን ንቡረ
ዐቢይ መንበር ።
ይቤለነ ዮም በቃለ በረከት ሥሙር ።
ለሕዝበ አሐቲ ኢትዮጵያ
ለእንተ ተዐቢ ሃይማኖት ክብር ።
አምጣነ ርትዕተ ለርቱዓን
ደቂቀ ዚአሃ ጻድቃን በፍናዊሃ ከመንሐር

ለ ዓ ለ ም

ተበሃሉሂ በአኀብሮ ሊቃውንቲሃ ለምድር ።
የሐውር በንጹሀ ወጽድቀ ይገብር ።
መልአከ ተክህኖ መድኅን መፈክረ
ሰላም ወፍቅር ።
እስመ ወልታ ጸብዕ ይቀጠቅጥ
ወቀስተ ኃያላን ይሰብር ።

እረ ጥሩ ጳጳስ ።

ደራሲ ለመሆን ስመኝ     ምነው እንደረጋው ቢጠ
ጡት ፤
ዘመን በቁሜ ቀብሮኝ ፤     ሳይነጣጠሉ በአንድነት ፡
መልአከ ምክሩ ገልጾልኝ፤     ተዋሕዶ ነው ሃይማኖት፤
እቀኛለሁ አሁን ስሙኝ፤
የጠማማ ሰው ጨዋታ፤     ቤተ ክርስቲያን ደህይታ
ብሰማው አይገባኝ ጠዋት
ማታ ፤
ስታነግሥ ኖረች ቀብታ ፡
አሁን ገባኝ ምሥጢሩ     ከእንግዲህ በቃት
አንተው ነህ ቅኔ     ማደግደጉ ፡
መምህሩ ፤     ለእራሷ ይሁን ማዕረጉ ፤
ብዙ ቅኔ አለኝ     ለሰሚው ግራ ነው
ብትሰሙት ፤     ይገርማል ፡
በመቃብሬ የጻፍኩት ፤     ጠላት ቢቀቡት መች
ያምራል ፡
በቢክ እየጻፍን እንኑር ፡     እራሷ ስትሄድ በጉንብስ ፡
ከእንግዲህ በቃ መቃብር     ዕድሜ ለመነች ለንጉሥ፡
የሚጠይቅ ካለ ደውሎ ፤     የዱሮ መሳፍንት ለጉ
ዳቸው ፡
ደራሲው ይደርሳል በቶሎ፡ ምርቱን እየበሉለራሳቸው
ነፍስና ሥጋ ተጣልተው፤የሰሞን መሬት ማለታቸው ፡
ይወቃቀሳሉ ተጋለው ፤ እነኝህ ሞኞች ያልተማሩ ፡
ያስታራቂ ያለህ የነፍስ ፤ መሬት በደወል የሚጠሩ ፡
እረ ጥሩ ጳጳስ ፤     ቀዳሹ እያለ ካህኑ ፤
በሰው አያልቅም ንትርኩ፤መሬት በድመት መወሰኑ ፤
አንተ አስታርቃቸው መልአኩ ፤ አይገርማችሁም
ወይ ለመሆኑ ፤
ቤተ ክርስቲያን ታማብን ፤     በገጠር ያለን ካህናት
ታጣጥራለች አሁን ፤
ጥሩ ጳጳስን ማለቷ ፤ ምንም አይቆጨን በእውነት ፡
ቅቤ ላይወጣው ሃይማኖት ፤

## ለብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የፓትርያርክነት ታሪካዊ ምርጫ የተደረሱ ቅኔዎችና ግጥሞች

### ሥላሴ ቅኔ

ከአለቃ መንክር መኰንን

ኢየሱስ ፍኖተ ጽድቅ መልአከከ ፊኑ ከመለሙሴ
ለተክለ ሃይማኖት ይኩኖ መራሒ ወከመ ይጺሕ
ፍኖቶ
እስመ ኮነ እንግዳ ዓለም ውጎደገ ቤቶ
ወቅድስናሁ ሀገር በዘኢ ክህለት ተከብቶ
በልሳነ ዮሐንስ ነበቦ
ቤተ ክርስቲያን ዘስዕነት ጠይቆቶ
ያስተዳሉ ዓቂበ መርዔቶ

### ኵልክሙ መወድስ ቅኔ

እምተክለ ሃይማኖት ዘዓርገ ተክለ ሃይማኖት
በምክያደ ወይንነ ቤቴል ከመይምላዕ በረከተ
ቤተ ክርስቲያን አቅረበት ዘቅድስናሁ መሥ
ፈርተ
አኮኑ አልጸቀ ለማዕረር
ዘተዘርዐ በአንብዐ ጺጋ ወፈረየ ምእተ
ሥርናየ አብርሃም ሃይማኖተ
ሐረስተ ወንጌል ይንሥኡ ዓስበ ፃማሆሙ
ቅድሳተ

### ለ ዓ ለ ም

ወለተክለ አሚን አስበ ፃማሁ በኀበ እግዚኦ ኢቤተ
እምገባዕተ ነግህ እስመ አቅደመ ዘገባዕተ ሠርክ
ጸውዖተ
ላእከ በዓለ ቤት ክርስቶስ ዘኢይሬኢ ገጻተ
እምገጸኤልያብ ከመሠምረ የውሀተ ዳዊት ዘተትሕተ

እኳከ ኣመአዘዘ ይንሣእ ሰብሐቲሆሙ ሀብታተ
እምገጸ ኤልያብ ከመሠምረ የውሃተ ዳዊት ዘተትሕተ

** ** **

## ኢትዮጵያ አፍሪ ካህን

ከይቁም ግዛው

ክርስቶስ ጠብቃት በምሕረት መቅደስክን
በጾም በጸሎትም ኢትዮጵያ አፍሪካህን
ብዙ ሰው ይገኛል በችሎቱ ላይ
እግዚአብሔርስ ችሎት ይኖር የለም ወይ ፥
ቀለማቸው ነካኝ ስትል ሰማሁህ ፥
ዓይን ካህን ነበር እኔም ፊት ያልኩህ
ጥፍጥሬ ቅብዓት ነው ባገራችን ላይ
ታዲያ ካህኑ ነው በጥፍ ጥሬ በይ ፥
ሰው የሚመረጠው በላብ ሥርቶ ነው
ሲሠራ አይቶ ላቡን መረጠው ይኸው ፥
ምን ጥበብ ቢሠራ ውል ውል ነው ልብሳችን
ምን ሞተር ቢተካ ለሸማኔ ዕቃችን
ዓርብ መን አይቀርም ዋናው መሣሪያችን ፥

ድሩ አልመጣም እንጂ ለንዲህ ያለ ጥበብ
እኔማ መን አለኝ ድሩ እንደዚህ ሲቀርብ ፥

ቤተ ክርስቲያን እጅግ ደስ ይበልሽ
በማመን ቢሠራ እንዲህ አማረልሽ
ተዋሕዶሽ አለ ፓትርያርክ ልብስሽ ፥

የወጡን እፍታ ሲልጥ ጌታ ጌታው
ለጭቁኑም ካህን ተሰጠው ከፍታው ፥

ሊቃውንቶቻችን ከቡራኖች ናቸው
ሁሉ እያጫፈረ አይዳፈራቸው

ሁሉም የለበሱት ባለኳስ ነው ካባው
ታዲያ ከቀለቡ አሁን ነው ማንጠሪያው
በዚያ በድንኳኑ ዋሻ በሆነው
አብርሃም እንግዳ ሲቀበል ምነው ?
አባ አይቀበሉም ከዋሻቸው ሰው ፥
ክርስቶስ እኔንም አምቶሃል አሉኝ
እነግርለታለሁ ላባቱ ታማኝ ፥
በእውቀት አንጹኝ ስትል ሰማሁህ
መልካም ብለሸኛል እሰይ ያንጹሕ ፥
መምህራንን በውቀት እያስተባበሩ
የመቅደሱን ዙሪያ ቅጽሩን ይገርግሩ
ልቅና ስድ አይሁን ዙሪያው በየደብሩ ።



www.ethiopianorthodox.org